

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን**

## ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ

## አጥቢ የዱር እንስሳትን በተመለከተ



# የተከናወነ

# የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2008ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ክፍል አንድ ........ 3
መግቢያ ........ 3
የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን አመሰራረት ........ 3
የባለስልጣኑ ራዕይ ........ 3
የባለስልጣኑ ዓላማ ........ 4
የባለስልጣኑ ተልዕኮ ........ 4
የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ........ 4
የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር ........ 5
የባለስልጣኑ የሰው ሀይል አደረጃጀት ........ 5
የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ ........ 6
የኦዲቱ አላማ ........ 6
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ........ 7
የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች ........ 7
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 8
የአሰራር ሥርዓት መግለጫ /Process description/ ........ 8
ክፍል ሁለት ........ 17
ግኝቶች ........ 17
ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ህገ-ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙ የመከላከል ስራ መስራቱን በተመለከተ፤ . 17
ባለስልጣን መ/ቤቱ ዓለምአቀፋዊ መስፈርት አሟልተው ........ 35
በዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት የተመዘገቡ ........ 35
የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች መስፈርቱን ጠብቀው ........ 35
እንዲተዳደሩ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 35
ባለስልጣን መ/ቤቱ የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብት ለማወቅ ........ 36
የሚያስችለውን አገራዊ የዱር እንስሳት ጥናትና ቆጠራ ........ 36
የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 36
ባለስልጣን መ/ቤቱ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ አጥቢ ........ 38
የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ለይቶ በማወቅ የልማትና ........ 38
የጥበቃ ስራ መስራቱን በተመለከተ፤ ........ 38
ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ........ 40
በሽታዎችን በተመለከተ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ........ 40
በጥናቶቹ ውጤት መሰረት የመከላከል እና ........ 40
የመቆጣጠር ስራ መስራቱን በተመለከተ፤ ........ 40

በባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ አመራር የውይይት መድረክ ስለመኖሩና ........................................................................44
በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ በመያዝ ተከታታይ .....................................................................44
ቁጥር ሰጥቶ በአግባቡ መያዛቸውን በተመለከተ፤ .............................................................................................44
በባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል በሚገኙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ......................................................45
ቦታዎች ላይ የሚሰራው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ስራ በተያዘለት .............................................................45
ጊዜ ስለመከናወኑና ክንውኑም በሪፖርት የተደገፈ ስለመሆኑ፤ ......................................................................45
በባለስልጣን መ/ቤቱ በመዋቅሩ መሰረት ቦታውን የሚመጥንና ....................................................................47
የተሟላ የሰው ኃይል መኖሩን በተመለከተ፤ ......................................................................................................47
ባለስልጣን መ/ቤቱ ለጥበቃ ቦታዎች የስርዓተ አያያዝ እቅድ (Managment plan) እንዲዘጋጅና እንዲተገበር የአሰራር ክፍተት ሲፈጥርም ............................................................................................................................................48
እንዲሻሻል ማድረጉን በተመለከተ፤ ...............................................................................................................48
ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፍቃድ አግኝተው የጥናትና ምርምር ስራ የሰሩ ተመራማሪዎች ዝርዝርና የሰሩት የጥናትና ምርምር ስራ..50
በባለስልጣን መ/ቤቱ መኖሩን በተመለከተ፤ ......................................................................................................50
በዱር እንስሳቱ መኖሪያ አካባቢ የሚዘረጉ መሰረት ..........................................................................................51
ልማቶች ላይ የተጽእኖ ግምገማ መደረጉን በተመለከተ፤ ..................................................................................51
በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ .............................................................................................................54
የመሰረተ ልማት ዝርጋታ መኖሩን በተመለከተ፤ ...............................................................................................54
የባለስልጣን መ/ቤቱ መረጃ መረብ ከተግባርና ኃላፊነቱ .....................................................................................59
ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን መያዙንና ........................................................................................................59
ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ...................................................................................................................59
ክፍል ሶስት ........................................................................................................... 61
የመደምደሚያ ሀሳቦች ....................................................................................................................61
ክፍል አራት ........................................................................................................... 65
የማሻሻያ ሀሳቦች ..........................................................................................................................65
አባሪ 1 ..................................................................................................................................... 1

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

## የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን አመሰራረት

1. በሀገራችን ለዱር እንስሳት ጥበቃ ማድረግ የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1901 ዓ.ም እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ባለው መልኩ መሰራት የተጀመረው ከአራት አስርት አመታት በፊት ነው፡፡ ይኸውም በ1956 ዓ.ም የሀገራችን የዱር እንስሳት ሀብት ይዘት በተመለከተ ጥናት ለማድረግ ከUNESCO መጥቶ የነበረው የጥናት ቡድን ለመንግስት ባቀረበው ሀሳብ መሰረት የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ጥበቃ እና ልማት ድርጅት በ1957 ዓ.ም እንዲቋቋም ከተደነገ ወዲህ ነው፡፡

2. መስሪያ ቤቱ ባለፉት አራት አስርት አመታት ጉዞው የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ለመጠበቅ፣ ለማልማትና በተገቢው መንገድ ለመጠቀም የሚያስችሉ የተለያዩ ቁልፍ ስራዎችን ያከናወነ ሲሆን፤ ካከናወናቸው ስራዎች አንዱ በሀገሪቱ ወካይ ምህዳረ-ቀጣናዎች አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶች በማካሄድ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ማቋቋም ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በአሁኑ ሰዓት 20 ብሄራዊ ፓርኮችና 4 የዱር እንስሳት መጠለያዎችን ጨምሮ ከ40 በላይ የተለያዩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በተለያዩ ጊዜያት እንዲቋቋሙ የተደረገ ሲሆን፤ በጥበቃ ቦታዎቹም አስፈላጊ የልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎች እየተከናወኑባቸው ይገኛል፡፡

3. መንግስት በተለይም ከቅርብ አመታት ወዲህ ለዱር እንስሳት ሀብት ልዩ ትኩረት በመስጠቱ ቀደም ሲል ለረጅም አመታት በስራ ላይ የነበሩ አዋጆች እና ደንቦች እንዲሻሻሉና መስሪያ ቤቱም በአዲስ መልክ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን (ኢ.ዱ.ል.ጥ.ባ) በሚል ስያሜ በአዋጅ ቁጥር 575/2000ዓ.ም በፌደራል ደረጃ እንዲደራጅ የተደረገ ሲሆን ተጠሪነቱም ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

## የባለስልጣኑ ራዕይ

4. ኢትዮጵያን በ2012 በዱር እንሰስሳት ቱሪዝም መዳረሻነት ከመጀመሪያዎቹ 5 የአፍሪካ ሀገራት አንዷ እንድትሆን ማድረግ፡፡

## የባለስልጣኑ ዓላማ

5. የአገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብት እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና ዘላቂነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

## የባለስልጣኑ ተልዕኮ

6. የኢትዮጵያ ዱር እንስሳትንና መኖሪያ አካባቢያቸውን በህብረተሰብና በባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ በሳይንሳዊ መንገድ በመጠበቅ፣ በማልማትና በማስተዋወቅ ለሀገራችን ህዝብ ብሎም ለአለም ህብረተሰብ ዘላቂ ስነ-ምህዳራዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግና ለመጭው ትውልድ በቅርስነት ማስተላለፍ ነው፡፡

## የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

7. ባለስልጣኑ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 575/2000 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡፡

- የዱር እንስሳት ሀብት ልማትን፣ ጥበቃንና አጠቃቀምን በተመለከተ የፖሊሲና የህግ ረቂቅ እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀዱም በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤
- በስሩ የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ህገ-ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙባቸው ይከላከላል፤
- በውጭ ቱሪስቶች ለሚከናወን አደን ፈቃድ ይሰጣል፤
- ሆቴል፣ ካምፕ፣ ሎጅና ሌሎች አገልግሎቶች በዱር እንሰሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ እንዲቋቋሙ ፈቃድ ይሰጣል፤
- ማናቸውንም የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ከአገር ለማስወጣት ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድና የጤና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
- የዱር እንስሳት ውጤት በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ ለተመለከተው ዓላማ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ ውጤቱንም ይለካል፤
- የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት እንዲመዘገቡ ለማስቻል ዓለማቀፋዊ መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ እነዚህኑ መስፈርቶች ጠብቀው መተዳደራቸውን ይከታተላል፤

- ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ የቴክኒክ እርዳታና ሌላም ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ ወገኖች ጋር ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመሰርታል፤
- የዱር እንስሳት ሀብትን አስመልክቶ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤ ለሚመለከታቸው ዓለም-አቀፍ ተቋማትም በየጊዜው ሪፖርት እያዘጋጀ ያስተላልፋል፡፡
- የዱር እንስሳትን በተመለከተ በማንኛውም ዓለም አቀፍ ስብሰባ ወይም ጉባኤ መንግስትን ይወክላል፤
- የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ጥናትና የስልጠና ፕሮግራም ያካሂዳል፤ ወቅታዊ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀነባብራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤
- ለክልሎች በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ረገድ አስፈላጊውን እገዛ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስልጣንና ተግባሩን ለሌሎች የፌደራልና የክልል መንግስት አካላት በውክልና ይሰጣል፤
- በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፤
- ከፌደራል መንግስት ጋር በተገባ የኮንሴሽን ውል መሰረት በግል ባለሀብቶች የሚተዳደሩትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ይቆጣጠራል፤
- በመንግስት በጸደቀ ተመን መሰረት ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፤
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር

8. ባለስልጣን መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆኖ ፣ በአንድ ዋና ዳይሬክተር እና በስሩ በሚገኙ ሁለት ጽ/ቤቶች እንዲሁም 13 ዳይሬክቶሬቶች ተዋቅሯል::

## የባለስልጣኑ የሰው ሀይል አደረጃጀት

9. በ2007በ.ዓ. በተገኘው መረጃ መሰረት ባለስልጣኑ 2029 በመዋቅር የተፈቀደና 971 በስራ ላይ ያለ የሰው ሀይል ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከኦዲት አካባቢው ጋር ተያያዥነት ያላቸው 6 ዳይሬክቶሬቶች ማለትም የዱር እንስሳት ንግድና ዝውውር ቁጥጥር ፣ የህብረተሰብ አጋርነትና የዱር እንስሳት ጥበቃ ትምህርት ፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ

ቦታዎች ልማትና ጥበቃ ፣ የዱር እንስሳት ጥናት ፣ ምርምር እና ጤና ፣ የብሄራዊ ፓርኮችና መጠለያዎች ማስተባባሪያ ፣ እና የዱር እንስሳት ገበያ ልማትና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬቶች 77 የተፈቀደ የሰው ኃይል ሲኖራቸው ከዚህ ውስጥ 56 በስራ ላይ ያለ የሰው ኃይል እና 21 ክፍት የስራ መደብ አላቸው፡፡

## የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ

10. የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት ከሚመደብ በጀት ሲሆን በጀቱና አጠቃቀሙ በሰንጠዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | ገቢና ወጪ | 2005ዓ.ም. | 2006ዓ.ም. | 2007ዓ.ም. |
|---|---|---|---|---|
| 1. | መደበኛ በጀት | 29,232,517.80 | 33,004,310.00 | 45,272,159.73 |
| | ካፒታል በጀት | 13,000,000.00 | 15,000,000.00 | 94,000,000.00 |
| | ድምር | **42,232,517.80** | **48,004,310.00** | **139,272,159.73** |
| 2. | መደበኛ ወጪ | 26,866,341.63 | 29,865,506.51 | (ከሐምሌ-ግንቦት) 39,523,660.26 |
| | የካፒታል ወጪ | 11,133,329.31 | 12,246,171.41 | 75,560,968.53 |
| | ድምር | **37,999,670.94** | **42,111,677.92** | **115,084,628.79** |
| በጀት አጠቃቀም በመቶኛ | | **90** | **87.7** | **82.6** |

## የኦዲቱ አላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ፣ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃን በተመለከተ ስራውን ለማስፈጸም የወጡ ሕጎችና ደንቦች ላይ በመመስረት ያወጣቸውን መመሪያዎችና የገባቸውን አለምአቀፍና አገርአቀፍ ስምምነቶች በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱ እና የተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ተፈፃሚ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ላይ የአሠራር ግድፈቶች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት የማሻሻያ ሀሣብ ማቅረብና ተጠያቂነትን ማስፈን ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

12. ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ሥር አራት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፡-

1. ባለስልጣን መ/ቤቱ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ልማትና ጥበቃ በወጡ ህጎች ፣ መመሪያዎች ፣ አለም አቀፍ እና አገር አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ቀልጣፋ እና ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤
2. ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች አይነት ፣ ብዛት እና የመኖሪያ አካባቢ /ሥርዓተ-ምህዳርን/ ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችል የጥናትና ምርምር ስራ መሰራቱንና ጥናቱ ያመጣው ውጤት የሚመዘንበት ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን መገምገም፤
3. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘና ወቅታዊ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ ፣ አስተዳደርና ስርጭት ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም
4. ባለስልጣኑ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥና በአካባቢው ለሚገኘው ህብረተሰብ እና በየደረጃው ላሉ ባለድርሻ አካለት የስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ በማድረግ ያመጣውን ውጤት የሚገመግም መሆኑን ማረጋገጥ፤

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

13. የኦዲት ቡድኑ አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን የመረጠ ሲሆን እነዚህኑ የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ ባለስልጣን መ/ቤቱን ለመገምገም የሚያስችሉ 39(ሰላሳ ዘጠኝ) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ለይቷል፡፡ ለተለዩት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችም ሊሆን የሚችል መደምደሚያ (Likely conclusion) ፣ የሚጠበቅ የማሻሻያ ሀሳብ (Expected recommendation) ፣ የኦዲቱን ዘዴ (Audit methodology) ፣ ለኦዲቱ የሚፈለጉ መረጃዎችን (Information Required) እና መረጃዎቹ የሚገኙበትን አካባቢ (Availability of information) የሚያሳዩ መግለጫዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

14. ኦዲቱ የሚከናወነው የመንግሥት መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሲሆን በኦዲቱ የሚሸፈነው ጊዜ ከ2005-2007ዓ.ም. በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ልማትና ጥበቃን በተመለከተ በተሰሩና እየተሰሩ ባሉ ስራዎች ላይ ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የሚከናወነው በባለስልጣን መ/ቤቱ ሲሆን ከኦዲት አካባቢው ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም በናሙና በተመረጡ ፣ በአማራ ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልል በሚገኙ በፌዴራልና በክልል መንግስት በሚተዳደሩ የጥበቃ ቦታዎች በአካል ተገኝቶ በማየት ፣ የሚፈለጉ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ እና ባለድርሻ አካላትን ጨምሮ ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ሲሆን፣

15. በባለስልጣን መ/ቤቱ አገልግሎት የሚያገኙ በፌዴራልና በክልል የሚገኙ ሃያ አራት የጥበቃ ቦታዎች ያሉ ሲሆን ፣ ከእነዚህ ውስጥ በተለያየ የስጋት ደረጃ ውስጥ ያሉ አጥቢ የዱር እንስሳት ያሉባቸው መሆኑ የሚታመኑ ሰባት የፌዴራልና የክልል የጥበቃ ቦታዎችን በአካል ተገኝቶ በማየት ፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና አስፈላጊ የሰነድ ማስረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የአሰራር ሥርዓት መግለጫ /Process description/

16. በባለስልጣን መ/ቤቱ ስራቸው ከኦዲት አካባቢው ጋር ተያያዥ የሆነ 6 ዳይሬክቶሬቶች ያሉ ሲሆን ፣ የየዳይሬክቶሬቶቹ ተግባርና ኃላፊነት (የስራ ድርሻ) እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ንግድና ዝውውር ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት፡-**

- የዱር እንስሳት በህገ-ወጥ መንገድ እንዳይታደኑና በህገ-ወጥ መንገድ እንዳይዘዋወሩ የሚቆጣጠር ግብረ-ኃይል ከፌዴራል እስከ ክልል፤ ቀበሌዎች ድረስ እንዲቋቋሙ ድጋፍ ማድረግ ፣ የተቋቋሙትንም የማብቃት ስራ ማከናወን፤
- የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን ንግድና ዝውውር በተመለከተ ሚስጥራዊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፤

- ድንበር ዘለል የዱር እንስሳት እና ውጤቶቻቸው ንግድ እና ህገ-ወጥ ዝውውር ቁጥጥር የላቀ ውጤት ካስመዘገቡ ሀገሮች ጋር ልምድና መረጃን መለዋወጥና ለአገሪቱ በሚበጅ መልክ ተግባራዊ ማድረግ፤
- የዱር እንስሳት ንግድን በሚመለከት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚወጡ የንግድ ልውውጥ ህጎች የሀገሪቱ ጥቅም ከማስጥበቅ አኳያ ያላቸውን ጠቀሜታ እያጠኑ ተግባራዊ ማድረግ፤
- ከህገ-ወጦች የተያዙት የዱር እንስሳት በህይወት ከሆኑ ወደ ተፈጥሮ መኖሪያቸው ወይንም መዋዕለ እንስሳት (zoo) እንዲለቀቁ ማድረግ፤
- በተለያዩ የሀገሪቱ መውጫ በሮች ወይም ጉምሩክ ኬላዎች እና ከክልሎች የተወረሱትን የዱር እንስሳት ውጤቶች ርክክብ ሲፈፀም የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት ፣ መረጃ በመያዝ ለሚመለከተው አለም አቀፍ ድርጅት(TRAFFIC) ፣ (CITES) እና ኢንተርፖል በየጊዜው ሪፖርት ማድረግ፤
- ህልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡ የዱር እንስሳት ንግድ ዝውውር በሀገሪቱና በዓለም አቀፍ ህጎች መሰረት እንዲካሄድ ማድረግ፤
- ለንግድ የተፈቀዱ የአገሪቱ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን በመለየት የንግድ ዝውውሩ በሀገራዊ እና አለም አቀፋዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ህጎች፣ ኮንቬንሽኖችና ስምምነቶች መሠረት መሆኑን መቆጣጠር፤
- ድንበር ዘለል ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት እና ውጤቶቻቸው ዝውውር ቁጥጥር ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በጋራ መስራት፤

**የህብረተሰብ አጋርነት እና የዱር እንስሳት ጥበቃ ትምህርት ዳይሬክቶሬት፡-**

- የማህበራዊ ምጣኔ ሀብት ጥናት (Socio economic survey) በማካሄድ፣ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥና በአካባቢው ከሚገኘው ህብረተሰብ ጋር ሰፊ ውይይት በማድረግና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራን በመስራት ስለጥበቃ ቦታው ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ህብረተሰቡን ማሳመን፤
- በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚኖረውን ህብረተሰብ ወቅታዊ ፍላጎት በማጥናት አመታዊ እቅድ ማዘጋጀት፤
- ከዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ተጠቃሚ እንዲሆን ለህብረተሰቡ የኢኮቱሪዝም ጥበቃ ቦታና የቁጥጥር አደን ቀበሌ በማቋቋም በማስጎብኘት እና በማሳደን ገቢ እንዲያገኙ በማገዝ በጥበቃ ቦታዎች ላይ የሚደርሰውን ጫና እንዲቀንስ ማድረግ፤

- ከለጋሽ ድርጅች ፈንድ በማፈላለግ ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ እንደ መንገድ ፣ የመጠጥ ውሃ ፣ ት/ቤት ፣ ጤና ኬላ የመሳሰሉትን መሰረተ ልማቶች መዘርጋት፤
- በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ለሚኖረው ህብረተሰብ የልምድ ልውውጥ የሚያደርግበትን መድረክ መፍጠር፤ ባህላዊ ምሽት በማዘጋጀት እና ቱሪስቶች ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍሉ በማድረግ ገቢ እንዲገኝ ማድረግ፤
- የአካባቢውን ህብረተሰብ ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ ልምዶችንና እውቀቶችን በመለየት ለዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ስራ በግብአትነት እንዲውሉ ማድረግ፤
- በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚገኙ ቁልፍ ባለድርሻዎችን መለየት ፤ በየደረጃው ማደራጀት ፤ ተግባርና ሀላፊነት በመለየት ቀጣይነት ያለው የምክክር መድረክ ማመቻቸት ፤ አማካሪ ጥምር ሀይል በየጥበቃ ቦታው አካባቢ ማቋቋም፤
- ስለ ሕብረተሰቡ አኗኗር ፣ ተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ፣ አሰፋፈርና ያላቸውን ተፅዕኖ እየተከታተሉ መፍትሄ መሻት፤
- ጠቃሚ የሆኑ የአካባቢ መተዳደሪያ ደንቦችን ከሀገራችን ህግና ደንቦች ጋር በማጣጣም ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- አገር አቀፍና አለም አቀፍ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ትስስር በመፍጠር ለጥበቃና ልማት ያላቸውን ሚና ማጉላት፤
- ወቅታዊ የትምህርት ማኑዋሎች እንደ አስፈላጊነቱ ፊልሞች ፣ ፖስተሮች በመሳሰሉት የትምህርት መስጫ ዘዴዎች በመታገዝ እንደየደረጃው ለአስጎብኚዎች ፣ ለባለሙያ አሳዳኞች ፣ ለህግ አስፈፃሚ አካላት ለስራ ሃላፊዎች ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችና በማስልጠኛ ማዕከላት ለሚገኙ የመከላከያ ሀይል አባላት ፣ ለት/ቤቶች ፣ ሕዝባዊ ማህበራትና በአገሪቱ የመግቢያና የመውጫ በሮች ኬላ ላይ ቁጥጥር ለሚያደርጉ ሰራተኞች የዱር እንስሳት ጥበቃ ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ትምህርቱን መስጠት፤
- የትምህርት ሂደትና አፈፃፀም ገምግሞ ግብረ-መልስ በማዘጋጀት አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ፤
- የዱር እንስሳት ጥበቃ ክበባትን በት/ቤቶች በማቋቋምና ትምህርት እንዲሰጥ ፣ በራሪ ፅሁፎችና መፅሄቶችን አዘጋጅቶ ማሰራጨት፤
- የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃ እና አጠቃቀም ማሰልጠኛ ተቋም እንዲቋቋም ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ክትትል ማድረግ፤

- የሰው ሀይል ስልጠና እቅድ በማውጣት ስካውቶችንና ሌሎች ባለሙያዎችን በተለያዩ የትምህርት ደረጃ የረዥምና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን ማመቻቸት፤
- ለቅድመ መከላከያ እርምጃ ያመች ዘንድ የግጭት መከላከያ ዘዴዎችን የያዙ ማኑዋሎችን መፅሄቶችን በራሪ ፅሁፎችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ማሰራጨት፤
- በተደጋጋሚ ጉዳት በሚያደርሱ የዱር እንስሳት ላይ ህብረተሰቡን በማሳተፍ መረጃ ማጠናቀርና እንደደረሰው የጥፋት መጠንና ክብደት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የረጅምና የአጭር ጊዜ የመፍትሄ ሀሳብ የያዘ ሪፖርት ማቅረብ፤
- የግጭት መንስኤዎችን መከላከል ፤ መቆጣጠርና መቀነስ የሚያስችል የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮን እንደአስፈላጊነቱ በሀገር ውስጥ እንዲተገበር ማመቻቸት፤
- ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና ተጨማሪ የሀብት ምንጮችን በማፈላለግ በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ለሚኖሩ ህብረተሰብ ክፍሎች አማራጭ የአኗኗር ስልቶችን መቀየስ፤

**የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ልማትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት፡-**

- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ብዛትና አይነት ላይ እንዲሁም ስለ ሥርአተ-ምህዳሩ ክትትል ማካሄድ፤
- በነባርና በአዲስ መልክ የሚቋቋሙትን የጥበቃ ቦታዎች በአለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት (IUCN) መስፈርት በሚያዘጋጀው ብሄራዊ ቴክኒካል ማኑዋል መሰረት በመገምገም የጥበቃ ቦታውን አይነት መወሰን ፤
- የጥበቃ ቦታዎችን ወሰን ምልክቶች ኖሯቸው ፣ ዳግም ክለላ ተደርጎላቸው ህጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸው መከታተል፤
- አዲሱ የጥበቃ ቦታ አለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ ይችል ዘንድ በአለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት (IUCN) እንዲያውቀው ማድረግ፤
- ሁሉንም ባለድርሻዎች ባሳተፈ መልኩ አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ መርሆዎችን የተከተለ የመሰረተ ልማት የማኔጅመንት ፕላን እንዲዘጋጅ በማስተባበር በየጊዜው ማሻሻል እና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤
- ከጎረቤት ሀገሮች አዋሳኝ የሆኑ የጥበቃ ቦታዎች ካሉ በጋራ ተቀናጅተው እንዲቋቋሙ፣እንዲለሙ እና እንዲተዳደሩ ማድግ(Transfrontier Protected Areas)፤
- ለጥበቃ ቦታዎች ማኔጅመንት አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን በመለየት እንዲዘረጉ ማስተባበር፤

- የዱር እንስሳቱን መኖሪያ ቦታ ሊቀንሱ የሚችሉ መጤ እና ወራሪ ዝርያዎችን ፤ የቁጥቋጦ መስፋፋትንና የሰደድ እሳትን መከላከል ፤ በቀላሉ ሊጎዱ የሚችሉ ስርዓተ-ምህዳሮች(Fragile ecosystem) ክትትል በማድረግ ተገቢውን የአያያዝ ሥርዓት መዘርጋት፤
- ተጨማሪ የሀብት ምንጮችን ማፈላለግ፤

**የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥናት ፣ ምርምርና ጤና ዳይሬክቶሬት፡-**

- ከፍተኛ የዱር እንስሳት ሀብት ክምችት እና አይነተ-ብዙ ስርአተ ምህዳር ያላቸውን ቦታዎች ማጥናት፤
- በሀገሪቱ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ዝርያዎችና (endemic) በእልቂት ስጋት ላይ ለወደቁት (Indangered) የዱር እንስሳት ዝርያዎች የተለየ ትኩረት በመስጠት ምርምሮችን ማካሄድ፤
- የጥናትና ምርምር መመሪያዎችን ማዘጋጀት፤ አፈፃፀማቸውን መከታተል፤
- በዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎች ላይ የሚቀርቡትን የጥናትና ምርምር ፕሮፖዛሎች መገምገም፤
- በዱር እንስሳት ምርምር ላይ ከሚሰሩ ዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን መዘርጋት ፤ በትግበራው ላይ መስሪያ ቤቱን ወክሎ መሳተፍ፤
- የስርዓተ ምህዳር ለውጥ ክትትል ስርዓት መዘርጋት ፤ ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤
- በዱር እንስሳት ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰሩ ባለሀብቶች የጥናትና ምርምር ድጋፍ መስጠት፤
- የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎች ላይ ዝርዝር ጥናትና ምርምር ማካሄድ፤
- በጥበቃ ቦታዎቹ ስነ-ምህዳር ትስስር ዙሪያ ምርምሮችን በማካሄድ ለማኔጅመንቱ የሚረዱ የመፍትሄ ሀሳቦች እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- የዱር እንስሳት በሽታዎች መከታተያና መቆጣጠሪያ ስርዓት መዘርጋት፤
- በዱር እንስሳት ጤናና በሽታዎች ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ፤ የጥናቶች ውጤት ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤
- ለዱር እንስሳት ጠመዳ ፣ Re-interodaction እና Translocation አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፤ አፈፃፀማቸውን መከታተል፤

- በዱር እንስሳት ስነ-ህይወት ፣ ስነ-ምህዳርና ጤና ዙሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ ጥቅም ላይ ማዋል፤
- የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተጨማሪ የሀብት ምንጮችን ማፈላለግ፤

**የብሄራዊ ፖርኮችና መጠለያዎች ማስተባባሪያ ዳይሬክቶሬት**

- በባለስልጣን መስሪያቤቱ ስር የሚተዳደሩ የጥበቃ ቦታዎች ተጠንተው እና ተዘጋጅተው የሚቀርቡ እቅድና ሪፖርቶችን ወዘተ.. ይዘት በማጥናት በመገምገም ለዋና ዳይሬክተሩ አስተያየትና የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል በቀጣይ በሚወሰዱ ተግባራት ላይ ለዋና ዳይሬክተሩ ያማክራል፣
- የጥበቃ ቦታዎችን የእለት ተዕለት የጥበቃ እንቅስቃሴ መረጃዎችን በየወቅቱ ማጠናቀር ፣ መተንተን ፣ በዱር እንስሳት ጥበቃ እስትራቴጂ መሰረት የተካናወነ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሲሆንም የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣
- በጥበቃ ቦታዎች ያሉት ዋርደኖች (ኃላፊወፖች) ባለሙያዎች የዱር እንስሳት ስካውቶች እና ሌሎች ሰራተኞች ፣ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ስልጠና የሚያገኙበትና ብሄራዊ ፓርኮችና የዱር እንስሳት መጠለያዎች ብቃት ባለው የሰው ሃይል የሚደራጁበትን መርሃግብር በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የጥበቃ ቦታዎቹን የአጭር እና የረጅም ጊዜ አፈፃፀም በሚመለከት ለጽ/ቤቱ የሚቀርበውን የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በቅድሚያ በመገምገምና ግልጽ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ማብራሪያ በመጠየቅ ለዋና ዳይሬክተሩ አስተያየቱን አክሎ ለውሳኔ ያቀርባል፣ ያማክራል በሚሰጠውም የአፈፃፀም መመሪያ መሰረት መፈፀሙን ይከታተላል፣
- የሀገሪቱ የዱር እንስሳት ተጠብቀውና ለምተው ለሀገሪቱ ልማትና እድገት ተገቢውን ድርሻ እንዲያበረክቱ ለማስቻል በሀገር አቀፍና በአለም አቀፍ ደረጃ ይበልጥ ስለሚታወቁበትና ስለሚስፋፉበት መንገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በማጥናት ተጠንተው የሚቀርቡትም ወቅታዊነታቸውን የጠበቁ መሆኑን በመመርመር ወቅታዊነት ባላቸው የልማት አቅጣጫዎች ዙሪያ ለውሳኔ የሚረዱ ሀሳቦችን በማመንጨት የበላይ አመራሩን ያማክራል፣

- ለጥበቃ ቦታዎቹ የእለት ተእለት የጥበቃ እና ልማት ስራዎች በዱር እንስሳት ጥበቃ እና ልማት መሪ እቅድ መሰረት የተከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሲሆንም የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወስዱ ማድረግ፣
- በጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ የቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎቹ ማኔጅመንት ፕላን መሰረት መሆናቸውን ኢንቨስትመንቶቹ የሚያሳድሩት የአካባቢ ተፅዕኖ ለማስወገድ እየተወሰዱ ያሉትን እርምጃዎች መገምገም አስፈላጊ እርምጃዎችንም መውሰድ፣
- በኢትዮጵያና በውጭ ሀገር መንግስታትና ተቋማት መካከል በዱር እንስሳት ነክ ጉዳዮች ላይ ስብሰባዎች ፣ ጉብኝቶች ፣ ውይይቶች ፣ ስምምነቶች ፣ ውሎች እና ድርድሮች ማድረግ በሚያስፈልግበት ጊዜ በቅድሚያ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የስራ ክፍሎች ወይም የስራ ኃለፊዎች በመያዝ አስፈላጊ መረጃዎች በማሰባሰብ ፣ ጥናትና ግምገማ በማከናወን ሊደረግ የታሰበው ጉዳይ ቢፈፀም ለሀገሪቱ ወይም ለተቋሙ የሚያስገኘውን አንፃራዊ ጠቀሜታ እና የአፈፃፀም አግባቡን በተመለከተ ዋና ዳይሬክተሩን ያማክራል፣
- ለለውጥ ትግበራው የሚያስፈልጉና ጠቃሚ የሆኑ የተለያዩ ሰነዶች የሚሰባሰቡበትን ከአቻ መስሪያ ቤቶችና ከሌሎች አካላት ምርጥ ተሞክሮዎች የሚገኙበትን መንገድ ያመቻቻል ፣ ያስተባብራል አጠቃላይ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱን የለውጥ ትግበራ ሂደት ከሚመለከታቸው የስራ ዘርፎች ጋር በጋራ በመገምገምጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገባቸው የማሻሻያና የማጠናከሪያ እርምጃዎችን የሚጠቁም የውሳኔ ሀሳብ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል በሚሰጠው ውሳኔና መመሪያ መሰረት መፈፀሙን እየተከታተለ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል ፣
- የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የጥበቃ ቦታዎች ጽ/ቤቶች የተቀላጠፈ አገልግሎት የሚሰጡበትንና በእቅዳቸው መሰረት የሚፈለገውን ውጤት የሚያስገኙበትን ፣ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች መካከል ሊኖር ስለሚገባው የስራ ቅንጅት እና መግባባት ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን አዳዲስ አሰራሮችንና የአፈፃፀም አግባቦችን በመቀየስ የውሳኔ ሀሳቦችንና አስተያየቶችን ያቀርባል በአፈፃፀም ሂደቶችም ላይ ያማክራል ፣ የሚሰጡ ውሳኔዎችንና አመራሮችን ተግባራዊነት እየተከታተለ እና እየገመገመ ሪፖርትና አስተያየት ያቀርባል ፣
- ሁሉም የጥበቃ ቦታዎች እና ሌሎች የስራ ክፍሎች የጎንዮሽ ግንኙነት ኖሯቸው በለውጥ ትግበራው አፈፃፀም ላይ ተሞክሮዋቸውን የሚለዋወጡበት መድረክ እንዲመቻቹ ያደርጋል

፣ መድረኩን በኃላፊነት ይመራል ፣ በለውጥ ትግበራው የሚታዩ የእውቀት ወይም ያመለካከት ክፍተቶችን በመለየት ከሚመለከተው የስራ ክፍል ጋር በጋራ በመስራት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችና የውይይት መድረኮች እንዲዘጋጁ ያደርጋል ፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል ፣

- የጥበቃ ቦታዎች ጽ/ቤቶችን በኃላፊነት ይመራል እንደአስፈላጊነቱ በሚሰጠው የፅሁፍ ውክልና መሰረት በቀጥታ ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ የሆኑ የሌሎች የስራ ሂደቶች ስራ ያስተባብራል ፣
- የጥበቃ ቦታዎቹን ጥበቃ እና ልማት ለማጠናከር አስፈላጊውን የበጀት እና የማቴርያል አቅርቦት እንዲሟላ ማድረግ አፈፃፀሙን መከታተል ፣
- በዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፣

## የዱር እንስሳት ገበያ ልማትና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት

- በዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ለሚነግዱ ፣ አዳኝ የዱር እንስሳትን በስፖርታዊ አደን ለሚያሳድኑ ፣ የዱር እንስሳት ለሚያረቡ እና ለሚይዙ ባለሀብቶች ፣ ባለስልጣኑ የሚያወጣቸውን መስፈርቶች ሲያሟሉ የድርጅትና የሙያ ፈቃድ መስጠት፤
- ፍቃድ የተሰጠው ባለሀብት ወይንም ባለሙያ ግዴታውን በአግባቡ መወጣቱን መከታተል እና መቆጣጠር፤
- የዱር እንስሳት ቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ዳር ድንበር ለይቶ ካርታ ማዘጋጀት፤
- በቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኙትን የዱር እንስሳት አይነትና ብዛት በማጥናት አመታዊ የአዳኝ ዱር እንስሳት ኮታ ማውጣት፤
- በሳይተስ የተመዘገቡ አዳኝ የዱር እንስሳት አመታዊ ኮታን ለሳይተስ ጽ/ቤት አሳውቆ ማስፈቀድ፤
- በቁጥጥር አደን ቀበሌ በመገኘት የአሳዳኝ ድርጅቶች በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን መወጣታቸውን ክትትልና ግምገማ ማድረግ፤
- የአደን ፍቃድ ጥያቄ ሲቀርብ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፤
- ቱሪስት አዳኞች የአደን መሳሪያቸውን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት እንዲችሉ ለአገር ውስጥ ደህንነት ዋና መመሪያ የፍቃድ ጥያቄ ማቅረብ፤

- አዳኝ ቱሪስት ለማደን ለጠየቃቸው አዳኝ የዱር እንስሳት ለያንዳንዱ በተቀመጠው ዋጋ እና በወቅቱ የውጪ ምንዛሪ ተመን መሰረት አስፈላጊው ክፍያ መፈፀሙንና የአደን መሳሪያ ማስገቢያ ፍቃድ መሟላቱን በማረጋገጥ ፍቃድ መስጠት፤
- ያደኑት የዱር እንስሳት በትክክለኛው አይነትና የመረጣ መጠን መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን ለንግድም ሆነ በሌላ ምክንያት በሀገር ውስጥ ወይም ከአገር ውጪ በሚዘዋወሩበት ጊዜ ጤንነታቸው እና አስፈላጊው የኳራንቲን ደንብ መሟላቱን ማረጋገጥና የጤና ሰርተፍኬት መስጠት ናቸው፤
- ለህጋዊ የዱር እንስሳትና ውጤቶች ወደ ውጪ መላኪያ ፍቃዶችን መስጠት፤
- አዳዲስ የህብረተሰብ አደን ቀበሌዎች እንዲቋቋሙ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤
- የባለሀብቶች የድርጅትና የሙያ ፍቃድ ማደስ፤
- ለዱር እንስሳት ፊልም ቀረፃ ፍቃድ መስጠት፤
- ለዱር እንስሳት ገቢያ ልማት የሚረዱ ተጨማሪ የሀብት ምንጮችን ማፈላለግ፤

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### <u>ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ህገ-ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙ የመከላከል ስራ መስራቱን በተመለከተ፤</u>

17. ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የማልማት፣ የማስተዳደርና ህገ-ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙባቸው የመከላከል ተግባርና ኃላፊነት በአዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

18. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከባለስልጣን መ/ቤቱና በናሙና ከተመረጡ የጥበቃ ቦታዎች ተሰብስቦ በተከለሰ ማስረጃ መሰረት ቀጥሎ በቀረቡት የጥበቃ ቦታዎች የልማትና የአስተዳደር ክፍተት መኖሩ እና ህገ-ወጥ ተግባራት እየተፈጸሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

19. ከጥቅ/2007-ጥር/2008ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሞ ብሔራዊ ፓርክ 3 በማጎ ብሔራዊ ፓርክ 2 በቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ 1 በአብጃታ ሻላ ብሔራዊ ፓርክ 1 በድምሩ 7 ስካውቶች በጥበቃ ስራ ላይ ተሰማርተው እያሉ የፓርኩን ሀብት ለመጠቀም በሚፈልጉ ህገ-ወጦች መገደላቸውና በባሌ ብሔራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ በህገ-ወጦች የተነሳውን የእሳት ቃጠሎ ለማጥፋት በተደረገው ርብርብ 1 ባለሙያ በእሳት ተቃጥሎ መሞቱን፣

20. ባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ በ1962 ዓ.ም. የተቋቋመና 6,987 ካሬ ኪ.ሜ. ስፋት ያለው ሲሆን፣ መጠለያው የተቋቋመው በጥርሱ ምክንያት ብርቅዬ የሆነውን ዝሆን ለመጠበቅ ነው፡፡ ሆኖም በመጠለያው የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

21. መጠለያውን በሚያዋስነው በኦሮሚያ ክልል በኩል ያለውን ተፋሰስ በመጠቀም የመስኖ እርሻ እየተስፋፋ መሆኑና የተሟላ መሰረተ ልማት ያላቸው ከ2,000 በላይ ህብረተሰብ መኖራቸው ፣ ለማስለቀቅም ከጥበቃ ቦታው አቅም በላይ መሆኑ፣

22. በክልሉ የሚገኙ አርብቶ አደሮች (የሱማሌ ክልል) እና አርሶ አደሮች (የኦሮሚያ ክልል) መካከል ያለ የአስተዳደር ችግር በመኖሩ መጠለያውን ከህገ-ወጦች ለመከላከል የመንግስት ጣልቃ ገብነት ከሌለበት በስተቀር ችግሩን መፍታት አዳጋች መሆኑና መጠለያው አደጋ ውስጥ መሆኑ፣

23. በመጠለያው ውስጥ 10 ኪሎሜትር ተገብቶ የውሃ ጉድጓድ በመቆፈሩ ውሃውን ፍለጋ የሚመጣ ማህበረሰብ መኖር ለመጠለያው ስጋት መሆኑ፣



በባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጥ ተብሎ ከመጠለያው ክልል 10 ኪሎ ሜትር ተገብቶ የተቆፈረ የውሀ ጉድጓድ

24. በአካባቢውና በውስጡ የሚኖር ማህበረሰብ በመጠለያው የሚገኘውን ደን በመጨፍጨፍ ለማገዶ ፣ ለከሰል እና ለቤት መስሪያ የሚጠቀሙ መሆኑ፣



በባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ በመጠለያው ክልል በ2007ዓ.ም እየተካሄደ ያለ የደን ጭፍጨፋ

25. ባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ በ1962 ዓ.ም. የተቋቋመና ከዳግም ክለላ በኂላ 2,150 ካሬ ኪ.ሜ. ስፋት ያለው ሲሆን በፓርኩ 78 አጥቢ የዱር እንስሳት ዝርያዎች (20ው

በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ) ፣ 310 የአዕዋፍ ዝርያዎች (6ቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ) ፣ 1600 የእጽዋት ዝርያዎች (160ው በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ) ፣ 40 ትናንሽ ወንዞች ያሉትና ለ12 ሚሊዮን ህዝብ ህይወት ዋስትና የሆነ ከየተራራው ስር የሚመነጩ ውሀዎች ያሉት በብዝሀ ሕይወት የበለጸገ ፓርክ ቢሆንም የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

26. በፓርኩ ለ40 እና ለ50 አመት ገደማ ሰፍረው እየኖሩ ያሉ ማህበረሰቦች ያሉ ሲሆን ሪራ በሚባለው ቀበሌ 450 አባወራ የሚኖሩበትና የተሟላ መሰረተ ልማት (ት/ቤት ፣ ጤና ኬላ ፣ መስኪድ ፣ የገበሬዎች ፋርም ትሬዲንግ ሴንተር) ያለው ፣ ጨፋ ዴራ በሚባለው ቀበሌ 100 አባወራ እንዲሁም በገራምባ ጉራ 200 አባወራ እየኖሩበት መሆኑና የእነዚህ ማህበረሰብ በፓርኩ መኖር በዱር እንስሳቱ መካከል የመኖሪያ መራራቅ (Habitat Fragmentation) እንዲኖርና በዚህም አንዱ አካባቢ የሚኖር የዱር እንስሳ ዝርያ ከሌላው ዝርያ ጋር እንዳይቀላቀል የሚያደርግ መሆኑና በዚህም ዝርያቸው ካልተዳቀለ የመጥፋትና በቀላሉ በበሽታ የመጠቃት እድላቸውን የሚያሰፋው መሆኑ፣



በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ የሚኖር ማህበረሰብ

27. በፓርኩ ህገ-ወጥ የደን ጭፍጨፋ ፣ የእርሻ መስፋፋት እና የቤት እንስሳቶቹ የዱር እንስሳቱ የሚመገቡትን የግጦሽ ሳር መጠቀም ያለ ሲሆን ከ700-800 ሺ.ህ የሚደርሱ የቤት እንስሳት በዱር እንስሳት መኖሪያ ክልል ውስጥ በመሰማራታቸው ወደፊት

ቁጥራቸው 1 ሚሊዮን ከደረሰ የግጦሽ ሳር ሊጠፋና የግጦሽ ሳሩ ሲጠፋ ደግሞ አይጥ ስለሚጠፋ ቀበሮዎቹ የሚበሉትን በማጣት ለጥፋት የሚዳረጉ መሆኑ፣



በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ በፓርኩ ክልል ለግጦሽ ተሰማርተው ያሉ የቤት እንስሳት

28. በ2010 በIUCN በተጠና ጥናት መሰረት የአደን መብዛት ፣ የመጠለያ እጦት እና የዱር እንስሳቱ መኖሪያ የተበታተነ መሆን በመካከለኛና ትላልቅ የዱር እንስሳት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፣

29. በማህበረሰቡ አካላት የሰደድ እሳት መከሰትና በሚነሳው እሳት ምክንያት በውስጡ የሚኖሩ የዱር እንስሳት አብረው መቃጠላቸው፣



በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ በ2007 ዓ.ም. በፓርኩ ክልል ተከስቶ የነበረና ለሰው ህይወት ማለፍ ጭምር ምክንያት የሆነ የእሳት ቃጠሎ

30. ፓርኩ በUNESCO እ.ኤ.አ ከ2009 ጀምሮ በጊዜያዊነት የተመዘገበ ቢሆንም በሰዎች ሰፈራና ንክኪ ምክንያት እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች ካልተቀረፉ በቋሚነት የመመዝገብ እድሉን እያጠበበው መሆኑ፣

31. በስመና ኦድቡሉ የቁጥጥር አደን ቀበሌ በ1993 ዓ.ም. የሚታደኑ የዱር እንስሳትን ለመጠበቅ የተቋቋመና 350 ካሬ ኪ.ሜ. ስፋት ያለው ሲሆን ፣ በጥበቃ ቦታው የሚከተሉት ችግሮች ተገኝተዋል፡-

32. ህገ-ወጥ የእርሻ መስፋፋት ፣ የግጦሽ መሬት መጠቀምና አደን በጥበቃ ቦታው መኖሩ ፣ የማደኛ ቦታ ይዞታዎች ከማንኛውም ህገ-ወጥ ተግባር መጠበቅ ማልማትና በቦታው ላይ ያሉትን የዱር እንስሳት ቁጥር እንዲጨምሩ በማድረግ ረገድ ክፍተት መኖሩ ፣ ኒያላዎች በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ አስጊ (critical) የእልቂት ስጋት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ተብሎ በIUCN ቀይ መዝገብ ውስጥ መመዝገባቸውና ኢትዮጵያ በIUCN እና በSITES ስምምነት መሰረት ኒያላዎችን ማደን እንድታቆም ትገደዳለች የሚል ሪፖርት መቅረቡ፣

33. ነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ በ1966 ዓ.ም. የተቋቋመና 514 ካሬ ኪ.ሜ. ስፋት ያለውና 90 የአጥቢ ፣ 351 የወፍ ፣ 42 የሬፕታይልስ ፣ 9 የአምፊቢያንስ እና 16 የአሳ ዝርያዎች ባለቤት ቢሆንም ከታች የተዘረዘሩ በርካታ ችግሮች አሉበት፡-

34. በፓርኩ ክልል ውስጥ በኤርጋንሳ ቀበሌ 759 ወንድ እና 62 ሴት በድምሩ 821 አባወራ እና እማወራ በቤተሰብ ደግሞ 3,414 ወንድ እና 246 ሴት በድምሩ 3,660 ቤተሰብ በህገ-ወጥ መንገድ ሰፍረው ያሉ መሆኑና በፓርኩ ክልል ውስጥ በሚገኘው የጫሞ ሀይቅ በቀን ከ50 እስከ 100 የሚያህሉ ህገ-ወጥ አሣ አጥማጆች ተሰማርተው ሁሉንም የአሳ አይነትና እድሜ በማጥመድ የአሳ ዝርያዎች እንዲመናመኑ ማድረጋቸው፣

35. በህገ-ወጦች በተከሰተው የእሳት ቃጠሎ በ2005 40 ሄክታር የሚሸፍን ፣ በ2006 ከ7 እስከ 8 ሄክታር እንዲሁም በ2007 እስከ 200 ሄክታር የሚሸፍን የሳርና የቁጥቋጦ ቦታ መቃጠሉ፣



በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ በፓርኩ ክልል በ2006 ተከስቶ የነበረ የእሳት ቃጠሎ

36. በህገ-ወጥ መንገድ የአገር ውስጥ አዳኞች ወደጥበቃ ቦታው በመግባት የተወሰኑ ዝርያዎችን እንደ ቆርኬ ፣ አጋዘን፣ የሜዳ ፍየል፣ ድኩላ፣ ድፈርሳ፣ ጉማሬ እና አንበሳ (ከብቶቻቸውን እንዳይበላ) እያደኑ መሆናቸውንና በፓርኩ በአመት እስከ 50 የሚደርሱ የዱር እንስሳት የሚታደኑ መሆኑን ፣ አደኑን ለመከላከል በስካውቶች በየቀኑ የቁጥጥር ስራ እየተሰራ ቢሆንም የቁጥጥር ስራው በበጀት ፣ በሰው ኃይልና በትራንስፖርት እጥረት ምክንያት ተከታታይና ሁሉን ቦታ የሚሸፍን ሊሆን አለመቻሉን፣




በ2006ዓ.ም. በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ በህገ-ወጥ መንገድ ለምግብነት የታደነ የሜዳ ፍየል

37. የፓርኩን ከግማሽ በላይ (52.5 በመቶ) የሚሸፍነው የፓርኩን ስያሜ ያገኘበት ሳራማና ሜዳማ የነጭ ሳር ሜዳ ከ500 በላይ አባወራዎች መኖሪያና ከ60 እስከ 70 ሺ በሚገመት የጉጂ አርብቶ አደሮች ህገ-ወጥ ሰፈራ እና ልቅ ግጦሽ የተጎዳና ሳሩም ሆነ የዱር እንስሳቱ በእጅጉ የተመናመኑ መሆኑ፣



በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ቀድሞ በነጭ ሳር ተሸፍኖ የነበረው የሳር መሬት ተራቁቶ

38. በሰረሞሌ ወንዝ አካባቢ በርካታ የኮሬ ማህበረሰብ አባላት ከፓርኩ ውጭ ቢኖሩም ወቅት ጠብቀው በመግባት በደን ምንጠራ ፣ በእርሻ መስፋፋት እና በአደን በደኑና በዱር እንስሳቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መገኘታቸው፣



በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ የሚገኘውን ደን በመመንጠር የተደረገ የእርሻ መስፋፋት

39. የአርባ ምንጭ ከተማና በዙሪያው ባሉ ወረዳዎች የሚኖር ህዝብ 95 ሺ ሜትር ኩብ የማገዶ እንጨት ፍላጎት ያለው በመሆኑ በየአመቱ ለ10 ሄክታር መሬት ደን

መጨፍጨፍ ዋነኛ ምክንያት መሆኑና በዚህም በየቀኑ በአማካይ 260 ሜትር ኩብ እንጨት በ650 ሰዎች በሁለት ዙር በየቀኑ ወደ ከተማዋ የሚገባ መሆኑና ደኑን ማራቆቱ፣



በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ ለከሰል፣ ለማገዶ እና ለቤት መስሪያ ሲባል የሚደረግ የደን ጭፍጨፋ፡



የሚጨፈጨፈው ደን የቀድሞ ሁኔታ

40. በከተማው ህዝብ የሚረቡ ነገር ግን አነስተኛ የወተትና የስጋ ምርት ያላቸው ከ50,000 በላይ ከብቶች በአባያ ሃይቅ ዳርቻና ዋሎ አካባቢ ያሉ ረግረጋማና ርጥበት አዘል መሬቶችንና ሳራማ አካባቢዎችን በእጅጉ እየጎዱ መሆናቸው እና በጫሞ ሴቶና በአካባቢው ከ3,000 እስከ 5,000 የሚደርሱ ከብቶች በፓርኩ ላይ ከፍተኛ ጫና በማድረስ ላይ መሆናቸው፣



በፓርኩ ክልል የቤትና የዱር እንስሳት በአንድ ላይ ለግጦሽ ተሰማርተው

41. ከመኖሪያ ቤት ግንባታ እና በጎርፍ ምክንያት ከከተማው በሚመጡ ቆሻሻዎች ደለል እንዲሁም ደግሞ በመጤና ወራሪ አረሞች የተፈጥሮ ሀብቱና የፓርኩ ገጽታ በከፍተኛ ደረጃ እተጎዳ መሆኑ፣

42. በፓርኩ በጫሞ ኃይቅ ሰሜናዊው ክፍል በቡሽ ላንድ ውስጥ የሚኖሩ የዱር እንስሳት በፓርኩ ድንበር ባለው የመኪና መንገድ ለመኪና አደጋ ተጋላጭ መሆናቸውና በ2005 ዓ.ም. ብቻ ሶስት ተራ ዝንጀሮ ፣ አንድ ድፈርሳና ሶስት ሬፐታይልስ መንገዱን ሲያቋርጡ መሞታቸው፣



በ2005ዓ.ም. በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ የፓርኩን ድንበር አቋርጦ በሚያልፈው መንገድ በመኪና አደጋ የሞተች ድፈርሳ

43. በፓርኩ ቀድሞ ያልነበረ የፕሮሶፒስ አረም እና ቆንጥር በእንጨት መሬት አካባቢው (wood land area) ላይ መብዛቱና በተለይ የቆንጥር አረሙ በአካባቢው ሳር እንዲበቅል የማያስችል በመሆኑ ሳር በል ለሆኑ እንስሳት የግጦሽ መሬት እንዲያጡና ቆንጥሩ እሾሀማና ጥቅጥቅ ያለ ከመሆኑ የተነሳ የዱር እንስሳቱን በውስጡ ለማለፍ የማያስችላቸው በመሆኑ ስጋት መፍጠሩን፣



በነጭሳር ብሄራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ ያለ የቆንጥር አረም

44. አዋሽ ብሄራዊ ፓርክ በ1958 ዓ.ም. የተቋቋመ፣ ከዳግም ክለላ በኂላ 590 ካሬ ኪ.ሜ. ስፋት ያለው እና 76 የአጥቢ ፣ 460 የአዕዋፍ ፣ 39 የሬፕታይልስ ፣ በኦዲቱ ወቅት ቁጥራቸው ያልታወቀ የአንፊቢያንስ እና የእጽዋት ዝርያዎች ያሉት ሲሆን በፓርኩ የሚከተሉት ችግሮች መኖራቸው ታውቋል፡-

45. የቤት እንስሳት ስምሪትን በተመለከተ የአካባቢው ማህበረሰብ አርብቶ አደር ስለሆነና ሌላ የግጦሽ አማራጭ ቦታ ስለሌለው 14 ቀበሌዎች ፓርኩ ላይ ጥገኛ መሆናቸውና ለግጦሽ የሚሰማራ የቤት እንስሳት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በሳር ተሸፍኖ የነበረው መሬት በግራር ዛፍ መቀየሩ፣



በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ በፓርኩ ክልል ለግጦሽ ተሰማርተው ያሉ የቤት እንስሳት

46. ፓርኩ የዱር እንስሳት መኖሪያ ሳይሆን የቤት እንስሳት መኖሪያ መሆኑ ፣ አንበሳ በራሱ መጠለያ ለመኖር የማይመች ሁኔታ ስለተፈጠረበት ፓርኩን ለቆ እየተሰደደ መሆኑ እና ፓርኩን በሚያቋርጠው መንገድ የሚያልፍ መንገደኛ የዱር እንስሳቱን በማብላት የተፈጥሮ የአመጋገብ ስርዓታቸውን ከማዛባቱም በተጨማሪ የዱር እንስሳቱ ለግጭት እየተጋለጡ መሆኑና የሚጣለውን ፌስታል በመብላት 4 ሳላዎች መሞታቸው፣



በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ከመንገደኛው ምግብ ፍለጋ ስትወጣ ከነልጇ በመኪና የተገጨች ዝንጀሮ

47. በከተማ መስፋፋት ምክንያት የአካባቢው ህዝብ በደጀን መሬት (buffer zone) ውስጥ እየገቡ መሆኑ ፣ በፓርኩ ውስጥ የሚኖሩት ህብረተሰቦች ቱሪስቶች ላይ ድንጋይ

መወርወር ፣ የተዘረጉት የኤሌክትሪክ ገመዶችን በጥሰው መብራት እንዲቋረጥ ማድረግ እና ሰራተኞች ተማረው ፓርኩን እንዲለቁ ማድረግ፣

48. የፕሮሶፒስ አረም እና ቆንጥር በእንጨት መሬት አካባቢው (wood land area) ላይ መብዛቱ ፣ የፓርቲኒየም አረም በሳራማ መሬቱ (grass land) ላይ መብቀሉና ሳሩ ተመልሶ ስለማይበቅል በአረም እየተሞላ መሆኑ ፣ ሳቫና የሳር መሬት (savanna grass land) የሚባለው የፓርኩ ክፍል አሁን በቁጥቋጦ እየተሸፈነ መሆኑ ፣ በየጊዜው መጠኑ እየጨመረ የሚሄደው የበሰቃ ኃይቅ የፓርኩ ትልቅ ስጋት መሆኑ፣

49. በፓርኩ የሳር መሬት እ.ኤ.አ በ2012 እና 2013 በአመት ውስጥ 8 ጊዜ የእሳት ቃጠሎ የነበረ መሆኑና ይህም ከሰል ለማክሰል ሲባልና በአካባቢው ያለው የአገዳ ምርት ሲቃጠል የተነሳ ይሆናል የሚል ግምት መኖሩ፣

50. በፓርኩ በሚያልፈው የመኪና መንገድ ፣ የባቡር መንገድና በሰዎች ሰፈራ ምክንያት የዱር እንስሳቱ መኖሪያ እየተከፋፈለና እየቀነሰ መሄዱ ፣ ለከሰል እና ለማገዶነት ለመጠቀም ሲባል የደን ጭፍጨፋ መኖሩ፣



በአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ በህገ-ወጥ መንገድ የሚሰራ የከሰል ማክሰል ስራ

51. በፓርኩ የቱሪስት ፍሰት ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ መምጣቱና የሚመጡትም ቱሪስቶች በፓርኩ የቤት እንስሳት ስምሪት ከመብዛቱ የተነሳ የዱር እንስሳቱን ከቤት እንስሳት መለየት እንዳልቻሉና በፓርኩ የሚያዩት ቱሪስቶችን ሳይሆን የአካባቢውን ማህበረሰብ መሆኑን መግለጻቸው፣

52. ሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ በ1958 ዓ.ም. የተቋቋመና 412 ካሬ ኪ.ሜ ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ ዳግም የተካለለ ሲሆን 22 ትላልቅና 13 ትናንሽ የአጥቢ የዱር እንስሳት ፣ 182 የአዕዋፍ እና 507 የእጽዋት ዝርያዎች እና ከባህር ወለል በላይ ከ3000 ጫማ በላይ ከፍታ ያላቸው 9 ተራራዎች ያሉት ሲሆን በፓርኩ የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

53. ፓርኩ በዩኔስኮ የአደጋ መዝገብ ውስጥ መመዝገቡና በፓርኩ ክልል በግጭ መንደር የሚኖሩትን የህብረተሰብ ክፍል በፍቃዳቸው ከፓርኩ ክልል ለማውጣት ጥናቱ የተጠናቀቀ ቢሆንም አፈጻጸሙ በመዘግየቱ ፓርኩን ከዩኔስኮ አደጋ መዝገብ ማስፋቅ አለመቻሉ፣

54. በፓርኩ ክልል ውስጥ የሰፈሩ ሰዎች ለግጦሽ በሚያሰማሯቸው የቤት እንስሳት ምክንያት የበሽታዎች መከሰት እና የመኖሪያ አካባቢ መቀነስ ለዱር እንስሳቱ ትልቅ ስጋት ሆኖ መቀጠሉ፣



በሰሜን ብሄራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ ተሰማርተው የሚገኙ የቤት እንስሳት

55. በአብጃታ ሻላ ብሄራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ ህገ-ወጥ እርሻና የት/ቤት ፣ የጤና ጣቢያና የመስጊድ መሰረተ ልማት ያለው ሰፈራ እየተስፋፋ መሆኑ እና በውስጡ የሚኖሩትን የህብረተሰብ ክፍሎች በዘላቂነት ከፓርኩ በማውጣት ለማስፈር ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ አለመከናወኑ፣

56. በአላጥሽ ብሄራዊ ፓርክ በፓርኩ ደጀን አካባቢ የህገ-ወጥ ሰፈራ ፣ እርሻ ፣ ግጦሽ ፣ አደን መስፋፋት እና ወቅት እየጠበቀ የሚከሰት የእሳት ቃጠሎ መኖሩ፣

57. በአላይደጌ የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል የአካባቢው አርብቶ አደሮች በህብረት የሜዳ አህያዎችን መግደል ፣ የተፈጥሮ ሀብቱ ተጠቃሚ መብዛት ፣ የጥበቃ ቦታውና እና የተፈጥሮ ሀብቱ ጥበቃ ከሰዎች ጣልቃ ገብነት የተከለለ አለመሆን ፣ የፕሮሶፒስ አረም በፍጥነት በመስፋፋቱ የዱር እንስሳቱ ምግብ እንዲያጡና የመኖሪያ አካባቢያቸው እንዲመናመን ማድረጉ ፣ ግሬቪ የሜዳ አህያ እና ሌሎች የዱር እንስሳት የግጦሽ መሬቱን የሚጠቀሙ ቢሆንም የአርብቶ አደሮች የግጦሽ መሬት መጠቀም እየጨመረ መምጣቱ ፣ የዱር እንስሳቶቹ መጠለያ መጨፍጨፍና አደን መኖር፣

58. በቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ ህገ-ወጥ የወርቅ ቁፋሮ መኖሩ እና ወደ 10,000 የሚጠጉ የወርቅ ቆፋሪዎች መኖራቸው ፣ የመጠለያ መጨፍጨፍ የዱር እንስሳቶቹ መብት መጣስ ፣ ቁፋሮው እስከ 35 ሜትር ጥልቀት ያለው ስለሆነና አደገኛ ገደል ስለሚፈጥር የዱር እንስሳቶቹ አደጋ ውስጥ መሆናቸው፣

59. በፓርኩ የእምነ በረድ ቁፋሮ በመኖሩ ምክንያት በሚፈጠሩ በዮችና ምቹ ያልሆኑ መንገዶች ምክንያት ዝሆኖችና ሌሎች የዱር እንስሳት ለመዝለል ሲሞክሩ ወድቀው የመሰበርና የመሞት አደጋ መኖሩ ፣ ለከሰል ምርት ሲባል የደን ጭፍጨፋ መኖሩ እና ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት አደን በፓርኩ ያለ ችግር መሆኑ ታውቋል፡፡

60. ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተጠቀሱት ችግሮች ትክክል መሆናቸውንና ማብራሪያ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

61. በባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ክልል ውስጥ የተቆፈረውን የውሃ ጉድጓድ በተመለከተ ፣ ለጊዜው ያለው አማራጭ ህብረተሰቡ ውሃ ፍለጋ ሲመጣ አካባቢው ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ መሆኑንና በረጅም ጊዜ ግን ለህብረተሰቡ ከብሔራዊ ፓርኩ ውጪ ውሃ የሚጎለብትበትን ሁኔታ መስራት ታሳቢ ሊደረግ እንደሚችል፣

62. በባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ የሚኖረውን ማህበረሰብ በተመለከተ ፣ በፓርኩ ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ በኦዲት ግኝቱ የተጠቀሱት ህብረተሰብ እንዲሁም

ያልተጠቀሱት ለግጦሽ ብለው ወቅትን ጠብቀው የሚመጡ ከብት አርቢዎች (ሰፈራና ልቅ ግጦሽ) እንዲሁም ከፓርኩ ውስጥ የአካባቢው ህብረተሰብ የሚፈልጋቸውን ሌሎች ሀብቶችን (ማር ፣ ሆራ ፣ ቡና ፣ ቀርከሃ ፣ ለመድሀኒትነት የሚውሉ እጽዋቶች) የሚጠቀም በመሆኑ ችግሮቹን ለመፍታት ጥናት ተደርጎ የሥርዓተ አያያዝ እቅድ(Management plan) በመዘጋጀት ላይ እንደሚገኝና በዕቅዱ መሰረት በአጭርና በረዥም ጊዜ ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣

63. የእሳት ቃጠሎ በአብዛኛው የሚከሰተው በፓርኩ ውስጥ ባሉ ህብረተሰቦች አማካይነት መሆኑን ፣ ይህም በተመሳሳይ መልኩ በቀጣይ የሚፈታና እስከዛ ድረስ ከህብረተሰቡ ጋር በመስራት ጥበቃና ቁጥጥር ማድረግ እና የቅድመ ክትትል የማስተማር ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን፣

64. ፓርኩን በዩኔስኮ መዝገብ ለማስመዝገብ እውቅና እንዲያገኝ የሚያስችሉ ቅድመ ሥራዎች በመከናወን ላይ የሚገኙ መሆኑንና የባሌ ታራራዎች ብሄራዊ ፓርክ የሥርዓተ አያያዝ ዕቅድ ሰነድ በዚህ አመት እንደሚጠናቀቅ ፣ የዚሁ ፓርክ የኖሚኔሽን ፋይል ለማዘጋጀት የሚረዱ ሥራዎች መሰራታቸውን ፣ ድራፍት የኮምፓራቲቭ አናላሲስ ዶክመንት ለአይዩሲኤን ተልኮ አስተያት እንደተሰጠበት ፣ ዶክመንቱም በዚህ አመት እንደሚጠናቀቅ ፣ በሚቀጥለው በጀት አመት እነዚህን ዶክመንቶች ለውሳኔ ለዩኔስኮ እንደሚልኩና በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ውስጥ በአለም መዝገብ ውስጥ መመዝገቡ ይጸድቃል ብለው እንደሚጠብቁ፣

65. በፓርኩ የሚሰማሩትን የቤት እንስሳት በተመለከተ፣ በሥርዓተ አያያዝ ዕቅዱ ውስጥ የልቅ ግጦሽን ለመቀነስና ብሎም ለማስቆም የሚያስችል ስትራቴጂ ማዘጋጀትና ሲጸድቅ ተግባራዊ ማድረግ ትልቁ ተግባር መሆኑንና እስከዛ ድረስ ግን ወቅት ጠብቀው የሚሰማሩትን የቤት እንስሳት ቁጥር በመቀነስ የግጦሽ ጫናውን ለመቀነስ ከህብረተሰቡ ጋር እየተነጋጋሩ መስራት አማራጭ መሆኑንና በዚሁ መልኩ እየሰሩ መሆኑን፣

66. የነጭሳር ብሔራዊ ፓርክ ክልል የሚኖሩትን ማህበረሰቦች በተመለከተ ፣ ከኢህአዲግ መግባት በፊት ከፓርኩ ውጪ አቡሎ አልፈጮ በሚባል አካባቢ ይኖሩ የነበሩና በ1983 ዓ.ም ወደ ፓርኩ ገብተው ላለፉት 24 ዓመታት በህገ-ወጥነት የሚኖሩ መሆኑንና በዚህ አመት ባለስልጣን መ/ቤቱ ፓርኩን መልሶ የማካለል ስራ ለመስራት ከኦሮሚያ ክልል ጋር በመነጋጋር ላይ እንደሚገኝና ከደቡብ ክልል ጋር በመወያየት ስምምነት ላይ መድረሱን ፣

የፓርኩም አስተዳደር ከአዋሳኝ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ጋር በፓርኩ ውስጥ የሚኖሩ ህብረተሰቦች የግጦሽ ጫናና እርሻ ማስፋፋት ሥራ እንዲቀንስ ስራ እየሰሩ መሆኑን፣

67. ህገ-ወጥ አሣ አጥማጆችን በተመለከተ ፣ የብሔራዊ ፓርኩ የውሃ ክልል 87 ካሬ ኪ.ሜ. (ከሁለቱ ሀይቆች ጫሞና አባያ ይጋራል) ለአሳ ፣ ለአዞ እና ለአእዋፋት መራቢያና መመገቢያ ፣ የጉማሬ መናኸሪያ በመሆኑ በተለይም ለቱሪዝም እንቅስቃሴ ወሳኝ መሆኑንና ክልሉ በብሔራዊ ፓርኩ ክልል የሚጠበቅ ቢሆንም ብዛት ያላቸው ህገ-ወጥ አሳ አስጋሪዎች እየገቡ እያጠፉት እንደሆነና ህገ-ወጥነቱን ለመከላከል የጥበቃና ቁጥጥር ሥራ ማጠናከር ፣ ለህብረተሰቡ አማራጭ የኑሮ ሁኔታን መፍጠር እና የሌሎችን መ/ቤቶች ትኩረትና ድጋፍ (ግብርና ቢሮ) የሚጠይቅ መሆኑን፣

68. የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ በከተማ መስፋፋት ምክንያት የአካባቢው ህዝብ በደጀን መሬት (buffer zone) ውስጥ እየገቡ መሆኑን በተመለከተ ችግሩ ትክክል መሆኑንና ለመፍታት ከክልልና ከከተማው አስተዳደር ጋር በመነጋገር ላይ ያሉ ቢሆንም ችግሩ ትኩረት የሚሻና ፣ የሁሉንም ግንዛቤና ድጋፍ የሚጠይቅ መሆኑን፣

69. ሳቫና የሳር መሬት የሚባለው የፓርኩ ክፍል አሁን በቁጥቋጦ እየተሸፈነ መሆኑ የሚለው በእርግጥ ትክክል ሆኖ ሳለ በ2007 በጀት አመት የተወሰነው በቁጥቋጦ የተሸፈነውን ይዞታ አላስፈላጊ ተክሎችን የማስነቀል ስራ የተሰራ በመሆኑ የተወሰነው ክፍል የማገገም ዕድል እንደሚኖረው፣

70. የፕሮሶፒስ አረም እና ቆንጥር በእንጨት መሬት አካባቢው (wood land area) ላይ መብዛቱ ትክክል መሆኑን ፣ ነገር ግን እነዚህን መጤ አረሞች በተመለከተ በመ/ቤታቸው አማካይነት ጥናት ተደርጎ በጥናቱ መሰረት ለማጥፋት ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣

71. የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ በዩኔስኮ የአደጋ መዝገብ ውስጥ መመዝገቡን በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባለፉት 2 አመታት በጣም ስኬታማ ከሆነባቸው ሥራዎች አንዱ የሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክን ከአደጋ መዝገብ /world heritage enedangered list/ ውስጥ ለማሰረዝ የሰራው ስራ መሆኑንና የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወኑን፡-

➢ በፓርኩ ውስጥ የሚኖሩ ከ418 በላይ አባወራዎችን አስፈላጊውን ካሳ በመክፈል እንዲወጡ የማድረግ ሥራ በተሳካ መልኩ በመጠናቀቅ ላይ እንደሚገኝ ፣ አማራጭ የከተማ ቦታ

በመስጠት ፣ ቀጣይ የኑሮ አማራጮችን በማፈላለግ ፣ በማጥናት የተሰሩ ስራዎች በህዝቡም በሌላም አካል ተቀባይነት ያገኘና የተሳካ እንደነበር፣

- በፓርኩ ውስጥ የሚያልፈውን ዋና የመኪና መንገድና ከዚሁ ጋር ተያያዥ የሆኑትንም የኤሌክትሪክ መስመር ከፓርኩ ውጪ እነዲሆን በመንግስት መወሰኑና ይህም ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን፣
- በፓርኩ ስርዓተ አያያዝ መሰረት የልቅ ግጦሽ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፣
- የቱሪዝም ማስተር ፕላን ተዘጋጅቶለት በዚሁ መሰረት እየተከናወነ መሆኑ የሚሉት ወሳኝ ስራዎችና ምንአልባትም በዚህ አመት የዩኔስኮ ሚሽን መጥቶ አረጋግጦና ለዩኔስኮ በሚላከው የአፈጻጸም ሪፖርት መሰረት ፓርኩ ከኢንዳንጀርድ ሊስት ውስጥ እንደሚወጣ ገልጸዋል፡፡

72. ሆኖም በተጠቀሱት የጥበቃ ቦታዎች ከታዩት አንጻር ችግሮቹ በወቅቱ የማይቀረፉ ከሆነና በጅምር ያሉ ስራዎች በአፋጣኝ የማይጠናቀቁ ከሆነ፣ በጥበቃ ላይ የተሰማሩ ስካውቶች ፣ የዱር እንስሳቱ እና የመኖሪያ አካባቢያቸው የወደፊት ህልውና ስጋት ላይ ይወድቃል፡፡

## ባለስልጣን መ/ቤቱ ዓለምአቀፋዊ መስፈርት አሟልተው በዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት የተመዘገቡ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች መስፈርቱን ጠብቀው እንዲተዳደሩ ማድረጉን በተመለከተ፤

73. ባለስልጣን መ/ቤቱ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት እንዲመዘገቡ ለማስቻል ዓለማቀፋዊ መስፈርት ማሟላታቸውን ሊያረጋግጥ እና እነዚህኑ መስፈርቶች ተጠብቀው መተዳደራቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

74. ሆኖም በናሙና የታዩ ሁሉም የጥበቃ ቦታዎች የሰዎች ሰፈራና ንክኪ ያለባቸው በመሆኑ መስፈርቶቹ ተጠብቀው እየተዳደሩ አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡

75. በጥበቃ ቦታዎቹ መስፈርቶቹ ተጠብቀው እንዲቆዩ ስላልተቻለበት ምክንያት የባለስልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው ቀድሞ ሲካለሉ የነበረው የህዝብ ቁጥር ትንሽ የነበረና ሰዎቹም ይለቃሉ በሚል እሳቤ የተቋቋመ መሆኑን ከተቋቋመ በኂላ ግን የሰው ቁጥር እየጨመረ

መሄዱን ፣ በህገ-ወጥ መንገድና ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ሲኖሩም አማራጭ ስለሌላቸው ወደጥበቃ ቦታው የሚገቡ መሆናቸውን ከጥበቃ ቦታው ለማስወጣት የተሰሩ ስራዎች ቢኖሩም ህዝቡ በተፈጥሮ ሀብቱ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ከሰው ንክኪ የጸዳ ማድረግ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

76. ሆኖም የጥበቃ ቦታዎቹ ከሰው ንክኪ የጸዱ አለመሆናቸው የተፈጥሮ ይዘታቸውን እንደጠበቁ እንዳይቆዩ የሚያደርግና እና በውስጡ በሚገኙት የዱር እንስሳት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር በመሆኑ ጉዳዩ እልባት አለማግኘቱ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ባለስልጣን መ/ቤቱ የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብት ለማወቅ የሚያስችለውን አገራዊ የዱር እንስሳት ጥናትና ቆጠራ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፤

77. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብት በአይነት ፣ በቁጥርና በመኖሪያ አካባቢ ለማወቅ የሚያስችለው አገራዊ የዱር እንስሳት ጥናትና ቆጠራ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

78. በዚሁ መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ በብሄራዊ ፓርኮችና መጠለያዎች፣ በአመት ሁለት ጊዜ (በደረቅና በእርጥብ ወቅት) እንዲሁም በቁጥጥር አደን ቀበሌ የአደን ኮታን ለመወሰን በየሁለት አመቱ የዱር እንስሳት ቆጠራ ለማድረግ ስርዓት የዘረጋ ቢሆንም ፣ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ቆጠራ ስለመደረጉ ባለስልጣኑ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ያቀረበው መረጃ፣

- ስራው ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅ በመሆኑ በአብዛኛዎቹ ጥበቃ ቦታዎች ጊዜውን የጠበቀ ቆጠራ አለመካሄዱን፣
- በዱር እንስሳት ዝርያ ቆጠራ ከጥበቃ ቦታዎች በያመቱ የተካሄደ ቆጠራ ፋይል በመፈለግ ለመሰብሰብ የተሞከረ መረጃ መሆኑን፣
- የቆጠራ ፋይል ከተገኙላቸው የአደን ቀበሌዎች ፣ ከተለያዩ ጥናቶችና የአየር ላይ ቆጠራዎች ለማካተት የተሞከረ መሆኑን እና
- ቆጠራው በክልል የሚተዳደሩትን እንዲሁም የቆጠራ ፋይል ያልተገኙላቸውን የጥበቃ ቦታዎች የማያካትት መሆኑን በመግለጽ የቀረበ ነው፡፡

79. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የጀርባ አጥንት ባላቸው በተለይም በጡት አጥቢ የዱር እንስሳትና በአእዋፍ ላይ በቂ የመነሻ መረጃ (Base Line data) እና አሁን ያለ መረጃ በእጃቸው እንደሚገኝ፣

80. በአጠቃላይ የዱር ህይወት ሃብቱ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም በአገር አቀፍ ደረጃ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ተገቢ በመሆኑ የተለያዩ መንገዶች የአየር ላይ ቆጠራም ጭምር በመጠቀም በአገር አቀፍ ደረጃ ከቀረቡት ሪፖርቶች የዱር እንስሳት ቆጠራ እየተደረገ መሆኑንና በዚሁም መሠረት፡-

- በዳግም ክለላ ወቅት የዱር እንስሳቱ ያሉበትን ሁኔታ በሚመለከት የዳሰሳ ጥናት መካሄዱን፣
- የሥነ-ምህዳራዊ ጥናት ክትትልና ኬዝ ቲም ሰው ኃይል ባላቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ በራሳቸው አቅም ቆጠራ በማካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን የራሳቸው አቅም ባልነበራቸው በቃፍታ-ሽራሮ ፣ አላይደጌ እና አዋሽ ላይ በዋና መ/ቤት በመታገዝ በቁልፍ ዝርያዎች ላይ ቆጠራ መካሄዱን፣
- በሌሎች የጥበቃ ቦታዎች ማለትም በቁጥጥር አደን ቀበሌዎች በየሁለት ዓመቱ ቆጠራ የሚካሄድ መሆኑን፣
- ልዩ ትኩረት በሚሹ እንደ ዝሆን፣ የኑቢያ ቀጭኔ፣ ነጭጆሮ ቆርኬ፣ መጋላ ቆርኬ ጎሽና አንበሣ በመሳሰሉት ቁጥራቸው ከ100 በላይ በሆኑ የዱር እንስሳት ላይ ኮላር በማሰር እንቅስቃሴዎቻቸውንና ስርጭታቸውን በተመለከተ በሣተላይት ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑን፣
- ህልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡት በቀይ ቀበሮ፣ የግሬቪ ሜዳ አህያ፣ የዱር አህያ፣ ዋሊያ እና የስዌይናይ ቆርኬ ያሉበትን ሁኔታ ተገቢው ክትትል ለመደረጉ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩ፣
- ህልውናው ለአደጋ የተጋለጠው የተኩላ (wild dog) እና በሥጋት ደረጃ የተቀመጡት የአቦ ሸማኔ እና አንበሳ የጥበቃ መርሃ-ድርጊት (Conservation Plan ) መዘጋጀቱን፣
- ሆኖም ባለው የአቅም ውስንነት ምክንያት በብሔራዊ ፓርኮችና መጠለያዎች በዕቅዱ መሠረት ቆጠራ የማይከናወን መሆኑን፣

- በነበረው የአደረጃጀት ችግርና የአቅም ውስኑነቶች ምክንያት ከላይ የተጠቀሱት የጥናትና ክትትል ሥራዎች ሪፖርቶች በመረጃ ቋት ተደራጅተው በተቋሙ ድረ-ገጽ እንዲጫን ያለመደረጉን፤
- ለአደጋ የተጋለጡ ግሬቪ የሜዳ አህያና የዱር አህያ ያሉበትን ሁኔታ የሚታወቅ ቢሆንም ይህን መሰረት በማድረግ የጥበቃ መረሃ ግብር (Conservation Action Plan) ያለመዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

81. ሆኖም ባለስልጣን መ/ቤቱ በየጥበቃ ቦታዎች ቆጠራዎች ሲደረጉና ካልተቆጠረም ያልተቆጠረበትን ምክንያት እየሰበሰበ በማጠናቀር ማስረጃውን በሶፍትና በሀርድ ኮፒ ይዞ አለማስቀመጡ ትክክል አይደለም፡፡

## ባለስልጣን መ/ቤቱ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ አጥቢ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ለይቶ በማወቅ የልማትና የጥበቃ ስራ መስራቱን በተመለከተ፤

82. ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉትና ትኩረት የሚሹ አጥቢ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን እንደ የስጋት ደረጃቸው (Critically endangered, Endangered, Vulnearable, Conservation, Near threatened and list concern) ለይቶ በማወቅ የማልማትና የጥበቃ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

83. በዚሁ መሰረት የኦዲት ቡድኑ በተለያየ የስጋት ደረጃ ላይ ያሉ አጥቢ የዱር እንስሳት ስለመኖራቸው ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፣ በናሙና ከተመረጡ የጥበቃ ቦታዎች እና ከሁለተኛ የመረጃ ምንጮች የተለያዩ መረጃዎችን አሰባስቦ በከለሰው መሰረት፡-

84. በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ኒያላዎች በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ አስጊ(critical) የእልቂት ስጋት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ተብሎ በIUCN ቀይ መዝገብ ውስጥ መመዝገቡንና በአባሽባ ደሞሮ ባለፉት አስርት አመታት መካካለኛ እና ትላልቅ አጥቢዎች በከፍተኛ ሁኔታ እየተጎዱ መሆኑና እስካሁንም ስጋቱ እንደቀጠለ መሆኑን፣

85. በነጭ ሳር ቆርኪዎች ከ1998 - 2000 ዓ.ም ቁጥራቸው 42 እንደነበረና በአደን ፣ በቀበሮ በመበላት እና በመዥገር ምክንያት 2 ብቻ መቅረታቸውን፣

86. በሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ቀይ ቀበሮዎች በእልቂት ስጋት ላይ ያሉ ተብሎ

በIUCN ቀይ መዝገብ ውስጥ መመዝገቡ፣

87. በአላይደጌ ጥብቅ ክልል ግሬቪ የሜዳ አህያ በአደጋ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበ መሆኑ፣

88. በኦሞ ብሄራዊ ፓርክ አመቱን ሙሉ አደን የሚካሄድ መሆኑና የአደኑ ተግባር አሁን በሚታየው አስፈሪ መልኩ የሚቀጥል ከሆነ የሜዳ አህያ ፣ ዝሆን ፣ መጋላ ቆርኬ ፣ ተኩላ ፣ ቀጭኔ ፣ ጎሽ ፣ ውድንቢና ሳላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊጠፉ እንደሚችሉ ስጋት መኖሩ ታውቋል፡፡

89. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፡-

90. በባሌ ተራራዎች ብ/ፓርክ ውስጥ የሚገኘውን የኒያላ ቁጥርን በሚመለከት፣

- እ.ኤ.አ በ2008------ 1136
- " " " በ2009 ----- 1125
- " " " በ2010 ----- 1052
- " " " በ2011 ----- 1720
- " " " በ2012 ----- 1592
- " " " በ2013 ----- 1672
- " " " በ2014 ----- 1784
- " " " በ2015 ----- 1974

እንደሆነ መረጃዎች የሚያመላክቱ ሲሆን ቁጥሩ የመጨመር እንጂ የመቀነስ ሁኔታ እንደማያመለክት፣

91. በስመና አደብሉ ቁጥጥር አደን ቀበሌ ያለው የኒያላ ቁጥር በተለያየ ወቅት የሚደረግ ቆጠራ እንደመሆኑ መጠን በየሁለት ዓመቱ የሚታየው አኃዝ መዋዠቅ ሊታይበት የሚችል ሲሆን፣ እ.ኤ.አ. በ2013 በተደረገው ቆጠራ ላይ የኒያላ (የደጋ አጋዘን) ቁጥር 939 ነው፤ በ2014 የተከናወነው ቆጠራ ግን በክትትልና ግምገማ ቡድን በመሆኑና የጋራ መግባባት ላይ ባለመደረሱ በያዝነው ዓመት በባለሙያዎች በሚደረገው ቆጠራ ውጤት ጋር ከተነፃፀረ በኋላ ተገቢው ስርአተ-አያያዝ እንዲዘረጋ እንደሚደረግ፣

92. የIUCN ቀይ መዝገብን በሚመለከት በኒያላ በተደረገው ቆጠራ መሠረት ቁጥሩ ላይ የመቀነስ ነገር ባይታይበትም በመኖሪያ አካባቢው ላይ የሚደርሰውን ጫናና በስርጭቱ ውስንነት ምክንያት በአደጋ መዝገብ ላይ እንዲካተት መደረጉን፣

93. የነጭ ሳርና የአዋሽ ቆርኬዎችን በተመለከተ፣ ቆርኬዎቹ በ1970ዎቹ አካባቢ ከስንቅሌ ወደ ሁለቱም ብሔራዊ ፓርኮች የተወሰዱ ሲሆን ገና ከጅምሩ የማጓጓዝና ወደ ቦታዎቹ የመውሰድ (Translocation) ሂደቱ ችግር የነበረበት በመሆኑ የቆርኬዎቹ በቦታው የመቆየት ዕድል አናሣ የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ የተቀሩትም በየጊዜው የተከሰተውን የሰው ሰራሽና የስጋ በል እንስሳት ጫና መቋቋም ባለመቻላቸው ሊጠፉና ቁጥራቸው ሊያሽቆለቁል የቻለ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚያደረገው ጥረት ጋር በቀጥታ ግንኙነት አለው የሚል እምነት እንደሌላቸው፣

94. በአላይደጌ ጥብቅ ክልል ያለው የግሬቪ የሜዳ አህያ በአደጋ መዝገብ የተካተተው የዛሬ ሰላሳ ዓመታት በፊት ሲሆን፤ ይህንን ሁኔታ ግምት በማስገባት ጥብቅ ክልሉ ወደ ብሔራዊ ፓርክ እንዲያድግ በማድረግ ላይ እንደሚገኙና ሳይከናወን የቆየው የዝርያው የጥበቃ መርሃ ግብር ዝግጅትም በቀጣይ ማዘጋጀት ለዱር እንስሳው ጥበቃ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጥ፣

95. በኦሞ ብሔራዊ ፓርክ ህገ-ወጥ የዱር እንሰሳት ግድያ በዋናነት የሚጠቀስ ችግር ቢሆንም በጥናቱ በተገለጹት ዱር እንሰሳት ላይ ተመሳሳይ ተፅእኖ ያስከትላል የሚል እምነት እንደሌላቸው ፣ ህገ-ወጥ አደንን በሚመለከት በዝሆን ላይ የሚፈጸመው ህገ-ወጥ ግድያ ትኩረት የሚሻና ዓለም አቀፍ ይዘትም ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

96. ሆኖም የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት አሰባስቦ በከለሳቸው ማስረጃዎች መሰረት በተለይም በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ውስጥ ካሉ አጥቢ የዱር እንስሳት ውስጥ የጥበቃ መርሀ-ድርጊት ያልተዘጋጀላቸው መኖራቸውና የተዘጋጀላቸውም አንዳንዶቹ በተያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ አፈጻጸም አለማግኘቱ ተገቢ አይደለም፡፡

## ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን በተመለከተ ጥናትና ምርምር በማካሄድ በጥናቶቹ ውጤት መሰረት የመከላከል እና የመቆጣጠር ስራ መስራቱን በተመለከተ፤

97. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን የመከላከል እና የመቆጣጠር ተግባርና ኃላፊነት በአዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

98. በመሆኑም በዱር እንስሳት መጠለያ ቦታዎች በሽታዎችን የመከላከል እና የመቆጣጠር ስራ ስለመሰራቱ በኦዲት ቡድኑ ሲጣራ፣

99. በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ የቀይ ቀበሮ እና ውሻ አብሮ መኖርና የተላላፊ በሽታ መከሰት ፣ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው የሚኖሩ አርብቶ አደሮች የግጦሽ መሬት ፍለጋ ሲንቀሳቀሱ ይዘዋቸው የሚንቀሳቀሱት ውሻዎች ያልተከተቡ በመሆናቸው በቀይ ቀበሮዎች ላይ አደጋ ማስከተሉና ለቀይ ቀበሮዎች ቁጥር መቀነስ ምክንያት መሆኑ ፣ የቀይ ቀበሮዎችን ቦታ ከቤት እንስሳት ንክኪ የፀዳ ባለመደረጉ ክትባት መጠቀም እንደአማራጭ መወሰዱና ክትባቱ በተደጋጋሚ በመሰጠቱ ቀበሮዎቹ የተፈጥሮ የመቋቋም ኃይላቸውን እያጡ መሆናቸው ፣ የእብድ ውሻ በሽታ መከላከያ መርሀ ግብር ሪፖርት መሰረት 25 ቀይ ቀበሮዎች በበሽታው ተጠቅተው መሞታቸውና በ6 እንስሳት ላይ የመጠቃት ምልክት መታየቱን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ታውቋል፡፡

100. እንዲሁም በፓርኩ ከቤት እንስሶቹ ጋር አብረው የሚሰማሩ ውሾች በመኖራቸው ቀበሮዎቹ በእብድ ውሻ በሽታ መያዛቸውንና በዚህም ምክንያት በበሽታው የሞቱ ቀበሮዎች ቁጥር በ1999ዓ.ም 40 እንዲሁም በ2007ዓ.ም. 26 እንደነበረና በሽታውን ለመከላከል ከባለስልጣን መ/ቤቱ በመጡ ባለሙያዎች እገዛ ለቀይ ቀበሮዎቹ ክትባት መሰጠቱን፣ ሆኖም ለበሽታው መከሰት ምክንያቶቹ ውሾች በመሆናቸው ንክኪው እስካለ ድረስ የበሽታው መከሰት አሳሳቢነቱ ቀጣይ መሆኑን የፓርኩ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

101. በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ አጥቢ የዱር እንስሳቶቹ በተለይም ዜብራዎች በበሽታ የሚጠቁ መሆናቸውን፣ በ2007ዓ.ም ብቻ 23 ዜብራዎች መሞታቸውንና የሚሰማሩበት የሳር መሬት ሳሩ ሲያድግ በሳሩ ጫፍ ላይ መዥገሮች የሚቀመጡና የሚያጠቋቸው መሆኑን ይህንንም መከላከል የሚቻለው የሳሩን ምድር እየከፋፈሉ በእሳት በማቃጠል እንደነበረ አሁን ግን በቤት እንስሳት ስምሪት አብዛኛው የሳር መሬት የተያዘ በመሆኑ መዥገሮቹን ማጥፋት አለመቻሉን፣ የቤት እንስሳት እና የዱር እንስሳት አብሮ መኖር ለዱር እንስሳት በሽታ መዛመት እና በበሽታ መጠቃት ዋና ምክንያት መሆኑን፣ የኩርንችት አረም በፓርኩ በመኖሩ የዱር እንስሳቱ እየበሉ በቀላሉ ሆዳቸው ተነፍቶ እንዲሞቱ ማድረጉንና በቀጣይም ትልቅ ስጋት መሆኑን ፣ በጫሞ ሀይቅ የአልጌ መጠን ሲጨምር ውሃውን ጠጥተው የሚሞቱ የዱር እንስሳት መኖራቸውንና በሽታው ይሄነው ለማለት ባይቻልም

ሌላም ምክንያት ሊኖር እንደሚችል የበሽታውን ምንነት ለማወቅ ሳይንሳዊ ጥናት ማድረግ የሚያስፈልግና ይህም በፓርኩ አቅም የማይቻል መሆኑን ፣ ለፓርኩ ኃላፊ ከቀረበው ቃለ-መጠይቅና ከፓርኩ በተገኝ የጽሁፍ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡



በ2007ዓ.ም. በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ በመኾገር ተይዞ የሞተ የሜዳ አህያ

102. በተጨማሪም በናሙና በታዩና በባለስልጣን መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ በሚደረግላቸው በሁሉም የጥበቃ ቦታዎች የዱር እንስሳቱን ከተለያዩ በሽታዎች ለመጠበቅና ለመከላከል የዱር እንስሳት ሀኪም የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

103. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በኦዲቱ በተመለከቱት በተወሰኑ የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ በዱር እንስሳት ላይ በተለይም በቀይ ቀበሮ እየደረሰ ያለው በእብድ ውሻ እና ተዛማጅ በሽታዎች የመጠቃት አደጋ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህንን ችግር ለመቅረፍ በዋናነት የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢ በሽታውን ከሚያስተላልፉ የቤት እንሰሳት ንክኪ ነፃ ማድረግ እንደሚገባ፣

104. አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ይህን ማድረግ ባለመቻሉ በአካባቢው የሚሰማሩ ውሾች ላይ ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር ክትባት በማካሄድ ላይ የሚገኙ መሆኑን፣ በቀይ ቀበሮዎች ላይ ሊተገበር የታቀደው ክትባት ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ በመሆኑ በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ለሙከራ ቁጥራቸው በጣም ውስን በሆኑ (አምስት ከመቶ በማይበልጡ) ቀበሮዎች ላይ የክትባት ሙከራ እንዲደረግ መፈቀዱንና እስከ አሁን ድረስ የቀይ ቀበሮ ክትባት እንደ መፍትሄ የተወሰደበት ሁኔታ አለመኖሩን፣

105. በነጭ ሣር ብሄራዊ ፓርክ በአንድ ወቅት የባርቾል የሜዳ አህያ መሞታቸው የሚታወቅ መሆኑንና የዚህ ክስተት ምክንያት ተብሎ የተገመተው የኩርንችት አረም በመብላታቸው ሊሆን እንደሚችልና በቀጣይ ጥናት ለማካሄድ በዕቅድ መያዙን፣

106. በጥበቃ ቦታዎች የዱር እንስሳቱን ከተለያዩ በሽታዎች ለመጠበቅና ለመከላከል የዱር እንስሳት ሀኪም የሌለ መሆኑን በተመለከተም በዱር እንስሳት በሽታ ላይ ክትትል እያደረገ ተገቢውን መረጃና የመፍትሄ ሃሳብ የሚያቀርብ ባለሙያ መኖር አስፈላጊ በመሆኑ በየጥበቃ ቦታው መደቡ የተቀረፀ ቢሆንም ክፍያውና ጥቅማጥቅሙ የሚስብ ባለመሆኑ ባለሙያዎችን ማግኘት አለመቻሉንና በየፓርኩ ያለውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት እንዲቻል የበሽታ ምልክቶች ሲታዩ ተገቢውን ክትትል በማድረግ በኩል በየጥበቃ ቦታው ያሉትን ባለሙያዎች በአማራጭነት በመጠቀም መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን የሚከሰቱት በሽታዎች ሊያደርሱት የሚችሉት አደጋ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ሲታመንበት ጉዳዩ የሚመለከታቸለው አካላት (ለምሳሌ፡- የአደጋ መከላከልን) እንዲያውቁት ተደርጎ ለመቀልበስ እንደሚሞከርና ለዚሁም ተሞክሮ እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

107. በተጨማሪም ለባለስልጣን መ/ቤቱ በቀረበው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በተሰጠ ምላሽ መሰረት በቀይ ቀበሮ ዙሪያ የቅድመ መከላከል ስራ መሰራቱንና በሽታዎች ሲከሰቱም አፋጣኝ መፍትሔ የሚፈለግ ሆኖ በአጠቃላይ አሁን ያለው አደረጃጀት /ተቋማዊ መዋቅር/ ባለስልጣኑ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አለመሆኑንና ይህም ከባለስልጣኑ አቅም በላይ መሆኑን ግንዛቤ መወሰድ እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

108. ሆኖም የዱር እንስሳቱ በበሽታ እንዳይጠቁ የቅድመ መከላከል ስራ አለመስራትና በሽታው ሲከሰትም አፋጣኝ መፍትሄ አለመፈለግ የዱር እንስሳቱ በበሽታ እየተጠቁ የመሄዳቸውን እድል ቀጣይ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም በተፈቀደው መዋቅር መሰረት የዱር እንስሳት ሀኪም በየጥበቃ ቦታው አለመኖሩ በሽታዎቹ በወቅቱ እየተለዩ አፋጣኝ መፍትሔ እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

**<u>በባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ አመራር የውይይት መድረክ ስለመኖሩና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ በመያዝ ተከታታይ ቁጥር ሰጥቶ በአግባቡ መያዛቸውን በተመለከተ፤</u>**

109. ባለስልጣን መ/ቤቱ መደበኛ እና ተከታታይ የስራ አመራር የውይይት መድረክ ሊኖረው እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ በመያዝ ተከታታይ ቁጥር ሰጥቶ በአግባቡ ሊይዝ ይገባል፡፡

110. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት ከ2005-2007ዓ.ም. ድረስ ያለውን ቃለጉባዬ ለመከለስ መረጃው ከባለስልጣን መ/ቤቱ ተጠይቆ የተገኘ ቢሆንም፣ ከ2005ዓ.ም. - ህዳር 2006ዓ.ም. ያለው ቃለጉባዬ በስራአመራሩ አባላት የተፈረመና በአግባቡ ተደራጅቶ የተቀመጠ ሲሆን ከታህሳስ 2006-2007ዓ.ም. ያለው መረጃ አጀንዳዎቹ የተቆራረጠ ሀሳብ የያዙና የአባላት ፊርማ የሌላቸው በመሆኑ ትክክለኛ ማስረጃ መሆናቸውን ማረጋገጥና በመረጃው ላይ ተንተርሶ ትንተና መስራት አልተቻለም፡፡

111. በተጨማሪም በ14/7/05ዓ.ም በተደረገ የአመራር አባላት ቃለጉባዬ በተገኘው መረጃ መሰረት ቃለ ጉባኤ መፈረም ሲገባው የማይፈረም መሆኑን ፣ ቃለ-ጉባኤ በወቅቱ ባለመፈረሙ ምክንያት እየተደራረበ መሆኑን፣ ለፊርማ በየስራ ክፍሉ ጠረጴዛ ላይ በመሰጠቱ የስራ-አመራሩ ሚስጥር እየባከነ መሆኑን እና አያያዙም ችግር ያለበት በመሆኑ መሻሻል እንዳለበት ተገልጿል፡፡

112. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በጊዜው ቃለ-ጉባዬውን ጽፎ ለማስፈረም ኃላፊነት ወስዶ የሚሰራ አካል ባለመኖሩ አሰራሩ ክፍተት የነበረበት መሆኑንና አሁን ግን የተሻሻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

113. ሆኖም ባለስልጣን መ/ቤቱ ከስራ አመራር አባላት ጋር የተደረጉ ቃለ-ጉባዬዎችን በመረጃነት አሰባስቦ አለማስቀመጡ በስብሰባው የሚነሱ መፍትሄ የሚሹ ጉዳዮች ወቅታዊ ምላሽ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ የማያስችለው በመሆኑና የመረጃ አያያዝ ክፍተትም በመፍጠሩ አሰራሩ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

## በባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል በሚገኙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ የሚሰራው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ስራ በተያዘለት ጊዜ ስለመከናወኑና ክንውኑም በሪፖርት የተደገፈ ስለመሆኑ፤

114. በባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል በሚገኙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ የሚሰራው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ስራ በተያዘለት ጊዜ መሰረት ሊከናወንና አፈጻጸሙ በሪፖርት የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡

115. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በጥበቃ ቦታዎች በየ3 ወሩ የክትትልና ድጋፍ ስራ በባለስልጣን መ/ቤቱ እንደሚሰራ በእቅድ የተያዘ በመሆኑ የሚደረገው የክትትል ፣ የድጋፍና ግብረ-መልስ ሥራ ወጥና ተከታታይ በሆነ መልኩ መሰራቱን ለማረጋገጥ መረጃው ከባለስልጣን መ/ቤቱ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

116. መረጃው ባይቀርብም በባለስልጣን መ/ቤቱ ድጋፍና ክትትል ስለመደረጉ ለማጣራት በናሙና በተመረጡ የጥበቃ ቦታ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለመጠይቅ መሰረት፣

117. ችግር ሲፈጠር ሄደው ከማየት በስተቀር በእቅዱ መሰረት ተከታታይነት ያለው ድጋፍና ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ወቅቱን ጠብቀው ቢልኩም ባጋጠሙ ችግሮች ላይ የሚሰጡ መፍትሄዎች ወቅቱን የጠበቁ አለመሆናቸውን፣ (ለባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

118. በየሁለት አመቱ ለኮታ ትመና ከዋናው መስሪያ ቤት እንደሚሄዱና ፣ አደን ሲኖር ለአደን ስካውት እንደሚልኩ፣ ከዚህ ሌላ የድጋፍ ስራ የማይሰራ መሆኑን፣ (ለበስመና አድቡሉ ጥብቅ ክልል ኃላፊ የቀረበ ቃለ-መጠይቅ ጥያቄ)

119. ከዋናው መስሪያ ቤት ሰው የሄደው የአዳባ ዶዶላ ማህበረሰብ አቀፍ ጥብቅ ክልል ሲካለልና፣ ለህጋዊ አደን ቆጠራ ለማድረግ በየአመቱ የሚታደነውን ኮታ ለመወሰን ብቻ እንደሆነ (ለአዳባ ዶዶላ ማህበረሰብ አቀፍ ጥብቅ ክልል ኃላፊ የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

120. ፓርኩ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ለባለስልጣን መ/ቤቱ የሚልክ መሆኑን፣ ሆኖም ባጋጠሙ ችግሮች መልስ የመስጠቱ ጉዳይ በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል እንደክፍተት የሚታይ መሆኑንና፣ በ2006 ዓ.ም አንድ ጊዜ ብቻ በሪፖርት አቀራረብ ላይ ግብረ-መልስ መስጠቱን፣ (ለነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

121. በቋሚነት እየሄዱ ድጋፍና ክትትል የሚያደርጉበት ሁኔታ አለመኖሩን፣ (ለአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

122. በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ ወቅት የጠበቀ አለመሆኑን ፣ ድጋፍን በተመለከተ የአቅም ክፍተቱን ለመሙላት የሚሰጡ ስልጠናዎች የሉም ማለት የሚያስችሉና በአግባቡ ሁሉንም ሰራተኛ ያማከለ ስልጠና የማይሰጥ መሆኑን ፣ የአፈፃፀም ሪፖርት ወቅቱን ጠብቀው ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እንደሚልኩና በሪፖርቱ ላይ የሚሰጥ ግብረ መልስ ግን አለመኖሩን (ለሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ) የየጥበቃ ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡

123. በተጨማሪም በባለስልጣን መ/ቤቱ የክትትል፣ የድጋፍና ግብረ-መልስ ሥራዎች ወጥና ተከታታይ በሆነ መልኩ አለመሰራታቸው እንደክፍተት መታየቱን እንዲሁም ከተሽከርካሪ አቅርቦት ችግር ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለሁሉም የጥበቃ ቦታዎች በታቀደው መሰረት የክትትልና ድጋፍ ስራ በአጥጋቢ ሆኔታ መፈጸም አለመቻሉን ከባለስልጣን መ/ቤቱ በቀረበ መረጃ የተገለጸ መሆኑን የባለስልጣን መ/ቤቱ የሰነድ ማስረጃ ያሳያል፡፡

124. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የድጋፍና ክትትል ስራቸው አጥጋቢ አለመሆኑንና ይህም የሆነበት ምክንያት የአቅም ክፍተትና የተሽከርካሪ ችግር እንደምክንያት የሚቀመጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

125. በተጨማሪም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገው ውይይትና በቀረበው ማስረጃ መሰረት ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት የተውጣጡ አመራሮች ለዳግም ክለሳ ስራና የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸውን የጥበቃ ቦታዎች በቦታው ተገኝተው በመመልከት ባለስልጣኑ በቀጣይ ሊሰራ ስለሚገባው ስራ አቅጣጫ እንዲያስቀምጥ አመላክተዋል፡፡

126. ሆኖም በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚደረገው የድጋፍ ፣ የክትትልና የግብረ-መልስ ስራ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አለመከናወኑ ችግሮችን በወቅቱ እየለዩ ለመፍታትና የተሻለ አሰራር ለማምጣት የማያስችል በመሆኑ አሰራሩ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

## በባለስልጣን መ/ቤቱ በመዋቅሩ መሰረት ቦታውን የሚመጥንና የተሟላ የሰው ኃይል መኖሩን በተመለከተ፤

127. ባለስልጣን መ/ቤቱ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ስራውን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችለውን የተሟላና ቦታውን የሚመጥን ባለሙያ (የሰው ኃይል) በመዋቅሩ መሰረት ሊያሟላ ይገባል፡፡

128. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት የባለስለልጣን መ/ቤቱ የ2007ዓ.ም. የሰው ኃይል መረጃ ተከልሶ በፌዴራል መንግስት የሚተዳደሩትን የጥበቃ ቦታዎችን ጨምሮ 2,029 በመዋቅር የተፈቀደ የስራ መደብ ያለው ሲሆን አሁን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ግን 971 ብቻ መሆኑና ይህም በመቶኛ ሲሰላ 46.5 መሆኑ ታውቋል፡፡

129. በናሙና በተመረጡ የጥበቃ ቦታዎች የሰው ኃይሉን በተመለከተ የየጥበቃ ቦታ ኃላፊዎች ለቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

130. የባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ በኢትዮጵያ ካሉ መጠለያዎች እና ብሄራዊ ፓርኮች ሁሉ ሰፊ ቢሆንም የቁጥርና ቦታውን የሚመጥን ባለሙያ እጥረት እንዳለበት ፣ በመዋቅር የተፈቀደ 124 የስራ መደብ ቢኖረውም ያለው የሰው ኃይል 43 ብቻ መሆኑ፣ (ለባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

131. በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ የተሻለ ደሞዝ ባለመከፈሉ እና ሰራተኛው ተጠቃሚ ባለመሆኑ 9 ስካውቶች መልቀቃቸውንና ሌላውም የተቀመጠው አማራጭ አጥቶ መሆኑን በፓርኩ በጀት የሰለጠኑና የስራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ፓርኩን ሳያገለግሉ የሚለቁ ሲሆን ይህም በፓርኩ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እያመጣ መሆኑን፣ ለፓርኩ 200 ስካውት የሚያስፈልግ ቢሆንም ያሉት ስካውቶች 76 ብቻ መሆናቸውን፣ (ለባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

132. በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ከሌሎች መስሪያ ቤቶች አንጻር ሲታይ ደሞዙ አናሳ መሆኑና በፓርኩ ከህገ-ወጦች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ጫና በመኖሩ የሰው ኃይል ፍሰት ማስከተሉን፣ ለስካውት መቅረብ ያለበት ጥቅማጥቅም (የውሃ ኮዳ፣ ስሊፒንግ ባግ፣ የዝናብ ልብስ የመሳሰሉት እና ከህገወጦች ቀድሞ ለመገኘት አስፈላጊ ትጥቆች

ስላልተሟሉ በሰው ኃይሉ ላይ አሉታዊ ጎን መፍጠሩን፣ (ለነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

133. በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ባለስልጣን መ/ቤቱና በአካባቢው ያለው የስኳር ፋብሪካ የሚከፍሉት ደሞዝ ከፍተኛ ልዩነት ያለው እና ስራው በራሱ ስጋት ያለበት ሆኖ እያለ ማበረታቻና የበረሃ አበል የሌለው በመሆኑ ቅጥር መፈፀም አስቸጋሪ መሆኑን፣(ለአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

134. በሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ የሰው ኃይል ፍሰቱ የተሻለ ቢሆንም ከሌሎች ተቋማት አንፃር የፓርኩ ደሞዝ አናሳ መሆኑና በፓርኩ የመልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ አስቸጋሪነት አንጻር ለስካውቶች የሚከፈል የውርጭ እና የአካባቢ (hard sheep area) አበል ባለመኖሩ ምክንያት የተሻለ ደሞዝና ጥቅማጥቅም ፍለጋ ስካውቶች እየለቀቁ መሆኑን፣ (ለሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ) የየጥበቃ ቦታው ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

135. የሰው ኃይሉን ለምን ሟሟላት እንዳልተቻለ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ በጥበቃ ቦታዎች ባለው ክፍት የስራ መደብ የሰው ኃይል ለሟሟላት በየጊዜው ማስታወቂያ እንደሚወጣና ቅጥርም እንደሚፈጸም ሆኖም ከገበያ ላይ የሰው ኃይሉን ለማግኘት በተለይ ክልል ላይ ያለው የደሞዝ ስኬል ፣ የበረሀ እና የውርጭ አበል ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ስኬል ጋር ያልተጣጣመ በመሆኑ ሰራተኛው አማራጭ ፍለጋ እንደሚለቅና ይህም ለስራው ትልቅ እንቅፋት መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡

136. ይሁንና ባለስልጣን መ/ቤቱ ከተጣለበት ሀገራዊ ኃላፊነት አንጻርና በተለይም በጥበቃ ቦታዎች የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች ከጉዳት ለመታደግና በአግባቡ ለመጠበቅ በዚህም የሚያስገኙትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማጉላት የሚያስችል የተሟላና ቦታውን በሚመጥን የሰው ኃይል አለመገኘቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ባለስልጣን መ/ቤቱ ለጥበቃ ቦታዎች የስርዓተ አያያዝ እቅድ (Managment plan) እንዲዘጋጅና እንዲተገበር የአሰራር ክፍተት ሲፈጥርም እንዲሻሻል ማድረጉን በተመለከተ፤

137. ባለስልጣን መ/ቤቱ ሁሉንም ባለድርሻዎች ባሳተፈ መልኩ አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ

መርሆዎችን የተከተለ የስርዓተ አያያዝ እቅድ እንዲዘጋጅና እንዲተገበር በአሰራር ላይ ክፍተት ሲፈጥርም እንዲሻሻል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

138. በኦዲቱ ወቅት በጥበቃ ቦታዎች የስርዓተ አያያዝ እቅድ መኖሩ እና ካለም የአሰራር ክፍተት ሲፈጥር ክለሳ እየተደረገበት ስለመሆኑ በመረጃ ክለሳና በቃለ-መጠይቅ ሲጣራ፣

139. ለአዋሽ ፣ ለአልጣሽ እና ለቃፍታ ሽራሮ ብሄራዊ ፓርኮችና ለሲንቅሌ ቆርኪዎች መጠለያ ፣ የስርዓተ አያያዝ እቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑ፣

140. የአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ የስርዓተ አያያዝ እቅድ የሌለውና ከዚህ በፊት የነበረው ያልተተገበረ መሆኑ፣ (ለአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

141. በባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ የተሰራ የስርዓተ አያያዝ እቅድ አለመኖሩ፣(ለባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

142. የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ከ2007-2017 እ.ኤ.አ የስርዓተ አያያዝ እቅድ ያለውና ሆኖም በስራ ሂደት በአሰራር ላይ ክፍተት በመፍጠሩና መስተካከል የሚገባው ጉዳይ በማጋጠሙ ክለሳ እየተደረገበት መሆኑ፣ (ለባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ)

143. የሰሜን ብሄራዊ ፓርክ የስርዓተ አያያዝ እቅድ 2009-2019 እ.ኤ.አ. የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡ የተቀመጡት መረጃዎች ከ2009 በፊት ያሉትን ያካተቱና ከ2009 እስከ አሁን ያሉትን በነ ገጽታዎች ያላከተቱ በመሆናቸው፣ ከ2009 ጀምሮ የተሰሩትን ስራዎች አካቶ እንዲሰራ ሀሳብ ያቀረቡ መሆኑን፣ (የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ ኃላፊዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ) ታውቋል፡፡

144. በጉዳዩ ላይ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቃፍታ ሽራሮ ፣ የጨበራ ጩርጩራ እና የስንቂሌ ቆርኪዎች መጠለያ የስርዓተ አያያዝ እቅድ ለማሰራት ጨረታ ወጥቶ በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን ፣ የአዋሽ እና የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርኮች የሥርዓተ አያያዝ ዕቅድ በቀጣይ በሚመጣ ፕሮጀክት ለማሰራት ታሳቢ መደረጉን፣

145. የባሌ ብሔራዊ ፓርክ የስርዓተ አያያዝ እቅድ ሰነድ ክለሳ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ መሆኑንና ቀሪ ስራዎቹ ከህብረተሰቡና በዞን ደረጃ ከሚገኙ ባለድርሻዎች ጋር ውይይት ማድረግ፣ ለስርዓተ አያያዝ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ ለከፍተኛ ባለስልጣናትና አመራሮች ተሞክሮ ልምድ ልውውጥ ዝግጅት ታሳቢ ተደርጎ በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ መሆኑን፣

- የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ የስርዓተ አያያዝ እቅድ ሰነድ በስራ ላይ የሚገኝና እየተተገበረ ያለ መሆኑንና በፓርኩ የቱሪዝም ማስተር ፕላን ተዘጋጅቶለት በዚሁ መሰረት እየተከናወነ መሆኑ የስርዓተ አያያዝ እቅዱም በሚቀጥለው አመት ዘመኑን ስለሚጨርስ በጀት ተይዞ የሚከለስበት ሁኔታ በእቅድ የሚያዝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

146. ሆኖም የስርዓተ አያያዝ እቅድ ለሌላቸው የጥበቃ ቦታዎች እንዲኖራቸው አለመደረጉና ወቅታዊ ክለሳ የሚያስፈልጋቸውም ክላሳው አለመደረጉ ፣ በእቅድ ላይ የተመሰረተ ወጥ አሰራር እንዳይኖር የሚያደርግና የአሰራር ክፍተት የሚፈጥር ነው፡፡

## ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፍቃድ አግኝተው የጥናትና ምርምር ስራ የሰሩ ተመራማሪዎች ዝርዝርና የሰሩት የጥናትና ምርምር ስራ በባለስልጣን መ/ቤቱ መኖሩን በተመለከተ፤

147. ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፍቃድ አግኝተው የጥናትና ምርምር ስራ የሰሩ የአገር ውስጥና የውጪ አገር ተመራማሪዎች ዝርዝርና የሰሩት የጥናትና ምርምር ስራ በባለስልጣን መ/ቤቱ በመረጃነት ሊጠበቅ ይገባል፡፡

148. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳትና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የጥናትና ምርምር ስራ የሚሰሩ የአገር ውስጥና የውጪ ሀገር ተመራማሪዎችን ፍቃድ ሲሰጥ ሊያሟሉ ከሚገባቸው መስፈርቶች አንዱ ጥናታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የጥናታቸውን ሶስት ቅጂ በመረጃነት ለባለስልጣን መ/ቤቱ ማስረከብ ነው፡፡

149. በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት በቀረበው መረጃ መሰረት ከ2010 እስከ 2015 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ለ210 የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ተመራማሪዎች የምርምር ሥራ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

150. ሆኖም የጥናትና ምርምር ስራውን ከሰሩ በኋላ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የጥናቱን ቅጂ የማያስረክቡ ተመራማሪዎች መኖራቸው ታውቋል፡፡

151. ስለዚሁ ጉዳይ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በተለይም የውጪ ሀገር ተመራማሪዎች በራሳቸው ፍቃደኝነት ሀገራቸው ከገቡ በኋላ የምርምር ስራውን እንደሚልኩና ከዛ ውጪ ግን የጥናቱን ቅጂ ሳያስረክቡ እንዳይወጡ የሚያደርግ የቁጥጥር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ሁሉንም ጥናቶች አሰባስቦ መያዝ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

152. በተጨማሪም ጉዳዩን በተመለከተ ለረቂቅ ሪፖርቱ በተሰጠ ምላሽ መሰረት በዱር እንስሳትና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ በአገር ውስጥና በውጪ ሀገር ተመራማሪዎች ስለተሰሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች የተሟላ መረጃ የሚይዙ መሆናቸውንና አብዛኞዎቹ የውጪ ሀገር ተመራማሪዎች የጥናቱን ውጤት ቅጂ ሳያስረክቡ የሚሄዱ መሆኑን፣ በፕሮጀክት ደረጃ ባሉት ላይ ግን በየአመቱ ያሉበትን ደረጃ በሚመለከት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ስለተገለጸላቸው ማቅረብ መጀመራቸውን፣ በቀጣይም ጉዳዩ ከውጪ ፖሊሲያቸው ጋር በማይጣረስ መልኩ መፍትሄ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

153. በመሆኑም በጥናቱ የቀረበውን ግኝትና ማሻሻያ ሀሳብ እንደግብዓት ተጠቅሞ ክፍተቶችን ለመሙላትና ተጨማሪ ጥናት ለሚያስፈልገው ጉዳይ ጥናት ለማድረግ አመላካች በመሆኑ ሁሉም አጥኚዎች የጥናትና ምርምር ስራቸውን ቅጂ ለባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያስረክቡ የሚያደርግ የቁጥጥር ስርዓት ተቀርጾ ተግባራዊ አለመደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡

## በዱር እንስሳቱ መኖሪያ አካባቢ የሚዘረጉ መሰረት ልማቶች ላይ የተጽእኖ ግምገማ መደረጉን በተመለከተ፤

154. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶች ከመዘርጋታቸው በፊት የተጽእኖ ግምገማ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

155. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በተሰበሰበ መረጃ መሰረት፡-

156. በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ዙሪያ ከሚገኘው ስኳር ፋብሪካ የሚወጣው ኬሚካል አዋሽ ወንዝን በመቀላቀሉ የውሀው ብክለት የዱር እንስሳቱን ህይወት አደጋ ላይ መጣሉ፣



ከመተሀራ ስኳር ፋብሪካ የሚወጣው ፍሳሽ ቆሻሻ በፓርኩ ክልል ያለውን የአዋሽ ወንዝ በክሎት

157. ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ፓርኩን አቋርጦ የሚያልፈው የባቡር መንገድ ሲሰራ ለዱር እንስሳቱ መሻገሪያ እንዲሆን ከስሩ የሚሰራ ማለፊያ መንገድ እንዲኖር ከባቡር ትራንስፖርት ኮርፖሬሽን ጋር የጋራ ስምምነት ቢኖርም በስምምነቱ መሰረት ባለመሰራቱ የዱር እንስሳቱ አዲሱን የሀዲድ መስመርና ቀድሞ የነበረውን ከአዲስ አበባ ጂቡቲ የአስፋልት መንገድ ማቋረጥ የግድ የሚላቸው በመሆኑ በእንስሳቱ ላይ የግጭት አደጋ ይበራከታል የሚል ስጋት ማሳደሩ፣

158. በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ በአካባቢው ከሚሰሩ የግንባታ ስራዎች የሚወጡ ቆሻሻዎች ወደ ወንዝ በመቀላቀላቸው የፓርኩን ቦታ ደለል እየሞላውና አካባቢው በመጤ አረም እየተያዘ መሆኑ ፣ ከአርባ ምንጭ ከተማና ከአካባቢው የሚወጣው የቆሻሻ ተፋሰስ ወደ ፓርኩ የሚለቀቅ በመሆኑ በተለይም የኩልፎ ወንዝ በደኑ ውስጥ መስመሩን ጥሎ በመግባት አካባቢውን መበከሉና ደኑንና የአዞ ገበያ አካባቢ የተፈጥሮ ገጽታው ላይ ጫና መፍጠሩና በፓርኩ በሚገነቡ መሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት ማድረሱ፣



ከኩልፎ ወንዝ ጋር ተቀላቅሎ ወደ ፓርኩ ክልል የሚገባ የአርባ ምንጭ ከተማ ቆሻሻ

159. በአብጃታ ሻላ ብሄራዊ ፓርክ የሶዳ አሽ ማምረቻ ፋብሪካው ከፓርኩ አጠገብ መኖሩ ለፓርኩ ህልውና አሉታዊ ተፅዕኖ መፍጠሩ፣

160. በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ የተጽእኖ ግምገማ ሳይሰራለት ከጎባ-ደሎ መና (ወረዳና ወረዳን የሚያገናኝ) የተሰራው ፓርኩን አቋርጦ የሚያልፍ የ110 ኪ.ሜ ርቀት ያለው መንገድ በመኖሩ የዱር እንስሳቱ በድምጽ ብክለት መረበሻቸውና ለመንገዱ ስራና ጥገና ሲባል የፓርኩን ሀብት እየተጠቀሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

161. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የትኛውም የመዋለ ንዋይ ፍሰት (Investment) ከመሰራቱ በፊት የአሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ ግምገማ የሚደረግ ቢሆንም አሉታዊ ጎኑን ለመቀነስ የተቀመጡትን አማራጮች መተግበራቸውን ለመከታተል ከዱር እንስሳቱ መኖሪያ ቦታዎች ይልቅ የሚሰራው የመዋለ ንዋይ ፍሰት ለነዋሪው ህዝብ አማራጭ የኖሮ ዘይቤን የሚያመጣለት በመሆኑ ከህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ ለመስራት ተቋማዊ መመጋገቡ አናሳ መሆኑ ለችግሩ መንስኤ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

162. ሆኖም ባለስልጣን መ/ቤቱ በአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት መሰረት የተለዩ አሉታዊና አዎንታዊ ጎኖችን መሰረት በማድረግ አዎንታዊ ጎኖችን ከማሳዳግ ባሻገር የአሉታዊ ጎኖችን ውጤት ለመቀነስ የተለዩ የማቃለያ መንገዶችን በወቅቱ እየተከታተለ ተግባራዊ እንዲሆኑ አለማድረጉ የዱር እንስሳቱንና የመኖሪያ አካባቢያቸውን አደጋ ውስጥ

የሚጥለው ይሆናል፡፡

## ዳግም ካለላ ለሚያስፈልጋቸው የጥበቃ ቦታዎች

## የዳግም ክለላ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤

163. ባለስልጣን መ/ቤቱ የወሰን ምልክቶች የሌላቸው የጥበቃ ቦታዎች ምልክት እንዲኖራቸው እና ዳግም ክለላ የሚያስፈልጋቸው እንደገና እንዲካለሉ ለማድረግ የክትትል ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

164. በዚሁ መሰረት በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የሰነድ ክለሳ ነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ፣ ኦሞ ብሄራዊ ፓርክና ባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ የዳግም ክለላ ስራ ባለመሰራቱ የጥበቃ ቦታውን ዳር ድንበር ከህገ-ወጦች ለማስጠበቅ አዳጋች መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

165. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ፣ ኦሞ ብሄራዊ ፓርክ ፣ ባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ እና ያንጉዲ ራሳ ብሄራዊ ፓርክ የድንበር ማካለል ስራዎችን ለማከናወን ጅምር ስራዎች እንዳሉ ፣ በእነሱ በኩል የዳግም ክለላ ስራ በዚህ አመት እንደሚጠናቀቅ ፣ በኦሞ ብሄራዊ ፓርክ ከግማሽ በላይ እንደተከናወነ ፣ ነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ከክልሎች ጋር ውይይት እንደተጀመረ ገልጸዋል፡፡

166. ሆኖም ዳግም ክለላ የሚያስፈልጋቸው የጥበቃ ቦታዎች ተካለው ወሰን ካልተበጀላቸው ስርዓተ አያያዝ ቀርጾ ተግባራዊ ለማድረግና ድንበሩን ከህገ-ወጦች ለመከላከል አዳጋች ይሆናል፡፡

## በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ

## የመሰረተ ልማት ዝርጋታ መኖሩን በተመለከተ፤

167. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የማያሳድር በእቅድ ላይ የተመሰረተ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ሊደረግ ይገባል፡፡

168. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት በጥበቃ ቦታዎች ሊኖሩ የሚገባቸው መሰረተ ልማቶች ተሟልተው ስለመገኘታቸው የኦዲት ቡድኑ በጥበቃ ቦታዎች በመገኘት እና የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ ባደረው ማጣራት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

169. በባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ በጽ/ቤቱ የመብራትና የውሃ ችግር በመኖሩ በስራ ላይ የስራ መጓተትና አላስፈላጊ ወጪ ማስከተሉ ፣ ለስካውቶቹም መብራት ፣ የውስጥ ለውስጥ

መንገድ እና መሻገሪያ ድልድዮች አለመኖራቸው፣

170. በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ በጥበቃ ቦታው ፓርኩን በቅርበት ለመከታተል እንዲቻል በቂ የስካውት ቤት አለመኖር ፣ (ሊኖር የሚገባው 14 ሲሆን አሁን ያለው ግን 6 ብቻ ነው) የካምፕ ሳይት ችግር መኖር ፣ (ቱሪስቶች ሲመጡ የሚያርፉበት 20 ካምፕ ሳይት ሊኖር ሲገባ አሁን ያለው 1 ብቻ መሆኑ) ፣ በፓርኩ በቂ ሎጅ አለመኖሩ፣ (8 ሎጅ የሚያስፈልግ ሲሆን አሁን ያለው ግን 1 ደረጃውን የጠበቀና አንድ ደግሞ ስራ የሚቀረው ሎጅ መሆኑ)

171. በበስመና ኦድቡሉ የቁጥጥር አደን ቀበሌ ውስጥ ፣ መንገድ እና ተገንጣይ የጥበቃ ካምፕ ያለመኖር ፣ በጥበቃ ቦታው ያሉት ሎጆች እና የቱሪስት ማደሪያ ቤቶች ደረጃቸውን የጠበቁ ባለመሆናቸው መንግስትም ሆነ ህብረተሰቡ ከአገልግሎቱ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እያገኙ አለመሆኑ ፣ 6 የስካውት መኖሪያ እና የእንግዳ ማረፊያ ቢያስፈልግም ያለው 2 ብቻ መሆኑና እሱም ዝናብ ሲዘንብ ደለል የሚገባበት መሆኑ ፣ የመሰረተ ልማት ግንባታ በጀት በወቅቱ አለመለቀቅ ፣ የተሰሩ ግንባታዎችን በወቅቱ ተከታትሎና አፈጻጸሙን ገምግሞ ቀሪ ስራዎች እንዲከናወኑ በዋናው መስሪያ ቤት በኩል ክትትል አለመደረጉ፣

172. በነጭሳር ብሄራዊ ፓርክ በፓርኩ ካለ 186 ኪሎሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገድ ውስጥ 50 ኪሎሜትር የእግር መንገድ ሲሆን ከቀረው 136 ኪሎሜትር ውስጥ አሁን አገልግሎት እየሰጠ ያለው ግን 25 ኪ.ሜ ብቻ መሆኑና እሱም ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ በደለል ስለሚሞላ መጠቀም አለመቻሉንና ለቱሪስቶች እንቅስቃሴ አዳጋች መሆኑን፣



በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ መኪና ማሳለፍ ያልቻለ የፓርኩ የውስጥ ለውስጥ መንገድ

173. በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ የመሰረተ ልማት በጀት በወቅቱ አለመለቀቁ ፣ ለሰራተኛው የሚሆን የመጠጥ ውሃ በሁሉም ካምፕ ሳይት አለመኖሩ እና ለሰራተኛው የመኖሪያ ቤት ችግር መኖሩ፣

174. በሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ የሳንቃ በር በሚባለው አካባቢ ያለው ሎጅ የስካውት ቤቶቹ ፓርኩ ሲመሰረት የተመሰረቱና ምንም አይነት እድሳት ተደርጎላቸው የማያውቅ መሆኑ ፣ ለመጠገን የበጀት እጥረት ማጋጠሙ ፣ የመጸዳጃ ቤቶቹ ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው ፣ በፓርኩ ውስጥ ያለው ወደ ጃን አሞራና በይዳ የሚወስደው መንገድ ላይ የመንገድ ትራፊክ ምልክት ባለመኖሩ በ2007 ዓ.ም 2 ሚኒሊክ ድኩላ እና 1 ሰስ የተገጩ መሆናቸው፣

175. ከዚሁ ጋር ተያይዞ በባሌ ተራራዎች የተሰራው የመኪና ፍጥነት መቀነሻ (Speed breaker) እና የትራፊክ ምልክት (Sign post) ለሌሎች የጥበቃ ቦታዎች በምርጥ ተሞክሮነት የሚጠቀስ ነው።




በባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ወደ ፓርኩ ክልል ሲገባ የሚታይ ምልክት (Sign post)

176. ፓርኩ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ያልተዘጋጀለት በመሆኑ ቱሪስቶችም ሆኑ ሌሎች የፓርኩ ተጠቃሚዎች ለምግብና ለመጠጥ ተጠቅመው የሚጥሏቸው እቃዎች ፓርኩን የሚያቆሽሹና የዱር እንስሳቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ መሆናቸው፣



በሰሜን ጨነቅ በሚባለው ቦታ የዱር እንስሳቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ የቆሻሻ መጣያ

177. ፓርኩ በአመት አስከ 23,000 ቱሪስት የሚያስተናግድ ቢሆንም በሳንቃ በር ያሉት 3 ሜትር ራዲየስ ስፋት ያላቸው 2 የምግብ ማብሰያ ቤቶች ብቻ መሆናቸውና እነሱም ደረጃቸውን ያልጠበቁ መሆናቸው ፣ ለቱሪስቶች የመመገቢያ አዳራሽ እና ማረፊያ ወንበር የሌለው መሆኑን ቦታው ተገኝቶ በማየትና ለቃለ-መጠይቅ ከተሠጡ መልሶች

ለማወቅ ተችሏል፡፡



በሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ለሚመጡ ቱሪስቶች ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀሙበት ቤት

178. እንዲሁም ከባለስልጣን መ/ቤቱ በተገኘው የሰነድ ማስረጃ መሰረት የዱር እንስሳት የመኪና ግጭት መኖሩንና የፍጥነት መቀነሻ ምልክቶችን ለማሰራት ከመንገዶች ባለስልጣን ጋር አብሮ ለመስራት እቅድ መያዙ ፣ በአብያታ ሻላ ብሄራዊ ፓርክ የመሰረተ ልማት ችግሮች መኖራቸው ፣ አልጣሽ ብሄራዊ ፓርክ ውስጥ በቂ የመሰረተ ልማት አቅርቦት አለመኖሩ ፣ በፓርኮች ውስጥ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ችግር መኖሩ ታውቋል፡፡

179. የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በጥበቃ ቦታዎች የመሰረተ ልማት ዝርጋታው የተሟላ አለመሆኑ እውነት መሆኑንና ለዚሁም የበጀት ማነስ ትልቁ ምክንያት መሆኑንና ለሚሰሩ መሰረተ ልማቶች የወጣ መለኪያ (Standard) አለመኖሩም ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

180. እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ ከባለስልጣኑ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ውይይት መሰረት ሁሉም ብሄራዊ ፓርኮች ጽ/ቤት የሚስፈልጋቸው ቢሆንም ጽ/ቤት ለሌላቸው ፓርኮች ግንባታ ለማካሄድ የበጀት እጥረት ማጋጠሙን ገልጸዋል፡፡

181. ሆኖም የመሰረተ ልማት መጓደል የጥበቃ ቦታዎቹ የሚሰጡትን አገልግሎት የተሟላ እንዳይሆንና ተገልጋዩን ምቾት የሚያሳጣ በመሆኑ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት አለመሰጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡

## የባለስልጣን መ/ቤቱ መረጃ መረብ ከተግባርና ኃላፊነቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን መያዙንና ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ፤

182. ባባስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ላይ የሚሰራውን የልማትና ጥበቃ ስራ በመረጃ መረቡ ላይ ሊያስቀምጥና ወቅታዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡

183. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብትና የመኖሪያ አካባቢ ለአለም በማስተዋወቅ ረገድ ሊጫወት የሚገባው ሚና የጎላ ከመሆኑ አንጻር ለዚሁ ስራ ከተግባርና ኃላፊነቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በዌብ ሳይት ድረ-ገጾቹ ላይ ሊያስቀምጥና ወቅታዊ ሊያደርጋቸው ይገባል፡፡

184. ይህንኑ ጉዳይ ለማወቅ የኦዲት ቡድኑ ኦዲቱን ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በሚያደርገው ማጣራት፣ የባለስልጣን መ/ቤቱ የመረጃ መረብ ከተግባርና ኃላፊነቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች የሌሉትና ያሉትም መረጃዎች ምንም አይነት ወቅታዊ ማስተካከያ ሳይደረግባቸው የቆዩ መሆናቸው ታይቷል፡፡

185. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብት ዓይነት ብዛትና ስርጭትን በተመለከተ በሳተላይት ክትትል የሚደረግባቸውን የዱር እንሰሳት የሚገኙበትን ልዩ ሥፍራ ለይቶ ማስቀመጥ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን እንደዚህ ዓይነቱ መረጃዎች በግልፅ ማስቀመጥ እንደማይቻል ጥቅል የዱር እንስሳት ሃብቱን መረጃ በሚመለከት ግን በመረጃ መረብ /ድረ-ገጽ/ ደረጃ ለተጠቃሚ ተደራሽ ማድረግ የሚገባው ቢሆንም የአይቲ የሥራ ክፍላችንንና የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬትም በቅርቡ የተዋቀሩ በመሆናቸው ቀደም ሲል ይህ አቅም ስላልተፈጠረና ድረ-ገጹም አገልግሎት ላይ ባለመዋሉ የዱር እንስሳት ሃብቱን የሚመለከትና በጥናትና ምርምር ግኝት የተመለከቱ የመፍትሄ ሃሳቦች በመረጃ መረብ አለመጫናቸውን፣ አሁን ግን በቂ ዝግጅት በማድረግ ላይ የሚገኙ መሆኑንና በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ማለትም በሳተላይት ኮላሪንግና በካሜራ ትራፒንግ እንዲሁም በG.I.S እና Remote sensing የተደገፈ መረጃ የመሰብሰብ ሥራዎች ማከናወን መጀመራቸው የዚሁ ጥረት ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

186. ሆኖም የባለስልጣን መ/ቤቱ የመረጃ መረብ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚጎበኝ በመሆኑ

ለስራው የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችን ሁሉ በማድረግ ተገቢ መረጃዎች ወቅታዊ እየተደረጉ አለመጫናቸው ተጠቃሚዎችን ከመረጃ ውጪ ያደርጋል።

# ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሀሳቦች

### 187. በጥበቃ ቦታዎች ህገ-ወጥ ተግባራት እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው፤

በተለያዩ የጥበቃ ቦታዎች ህገወጥ ተግባራት ስለመፈጸማቸው ለማጣራት ኦዲት ተደርጎ በዝርዝር የኦዲት ግኝቶች ላይ የተመለከቱት ጉልህ የሆኑ ችግሮች ታይተዋል፡፡
እነርሱም፡-

- ከጥቅ/2007-ጥር/2008ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሞ ብሔራዊ ፓርክ 3 በማጎ ብሔራዊ ፓርክ 2 በቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ 1 በአብጃታ ሻላ ብሔራዊ ፓርክ 1 በድምሩ 7 ስካውቶች በጥበቃ ስራ ላይ ተሰማርተው እያሉ የፓርኩን ሀብት ለመጠቀም በሚፈልጉ ህገ-ወጦች መገደላቸውና በባሌ ብሔራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ በህገ-ወጦች የተነሳውን የእሳት ቃጠሎ ለማጥፋት በተደረገው ርብርብ 1 ባለሙያ በእሳት ተቃጥሎ መሞቱ፣
- በሁሉም የጥበቃ ቦታዎች በህገ-ወጥ መንገድ የሚፈጸም ግጦሽ ፣ ደን ጭፍጨፋ ፣ አደን ፣ ከሰል ማክሰል ፣ ሰፈራ እና የእርሻ መስፋፋት፣
- በአንዳንድ የጥበቃ ቦታዎች ላይ በህገ-ወጦች የሚነሳ የእሳት ቃጠሎ፣
- በአንዳንድ የጥበቃ ቦታዎች ላይ ህገ-ወጥ የመሳሪያ ዝውውር መኖና ይህም በፓርኩ ጥበቃና ቁጥጥር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣
- በወንዝ ተፋሰስ አካባቢ ያሉ የጥበቃ ቦታዎች የአካባቢው ህብረተሰብ የተፋሰስ ልማትን በመጠቀም የመስኖ እርሻ እያስፋፉ መሆናቸውና ይህም በጥበቃ ቦታው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፣

### 188. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት ያስቀመጠውን መስፈርት ያሟሉ ስለመሆናቸው፤

በተቀመጠው ዓለም አቀፋዊ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት መስፈርት መሰረት የጥበቃ ቦታዎቹ ከሰው ንክኪ የጸዱ ባለመሆናቸው ምክንያት የተፈጥሮ ይዘታቸውን እንደጠበቁ እንዳይቆዩ እና በውስጡ በውስጡ በሚገኙት የዱር እንስሳት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር መሆኑ፣

189. **የዱር እንስሳት ሀብትን በተመለከተ፤**

በአንዳንድ የጥበቃ ቦታዎች በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የዱር እንስሳት ቆጠራ አለመደረጉና ቆጠራ ከተደረገበትም የጥበቃ ቦታ መረጃው በባለስልጣን መ/ቤቱ ተሰብስቦና ተጠቃሎ በመረጃነት የማይቀመጥ መሆኑን፣

190. **ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ አጥቢ የዱር እንስሳትን በተመለከተ፣**

ባለስልጣን መ/ቤቱ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉትን ሁሉንም አጥቢ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ካሉበት የስጋት ደረጃ (Critically endangered, Endangered, Vulnearable, Conservation, Near threatened and list concern) ለማውጣት የያዘው የልማትና የጥበቃ እቅድ ተግባራዊ አለመደረጉና ለልማት ስራው በእቅድ ያልተያዙም የዱር እንስሳት መኖራቸው፣

191. **በበሽታ የተጠቁ አጥቢ የዱር እንስሳት መኖራቸውን በተመለከተ፤**

በዱር እንስሳቱ ላይ የሚከሰት በሽታ መኖሩ እና በሽታው አሁን ባለው ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ በተለይም በእልቂት ስጋት ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ህልውና አስጊ ሁኔታ ውስጥ መውደቁን ፣ በተጨማሪም የዱር እንስሳት ሀኪም በየትኛውም የጥበቃ ቦታ ባለመኖሩ የበሽታውን መንስኤ በማጥናት የመከላከልና የመቆጣጠር ስራው ላይ አሉታዊ ጎን መፍጠሩን፣

192. **የባለስልጣን መ/ቤቱን የስራ አመራር አባላት ቃለ-ጉባዔ በተመለከተ፤**

በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ከቀረበው የ3 ዓመት ቃለጉባዔ (ከ2005-2007ዓ.ም.) ውስጥ ከታህሳስ 2006-2007ዓ.ም. ያለው መረጃ አጀንዳዎቹ የተቆራረጠ ሀሳብ የያዙና የአባላት ፊርማ የሌላቸው በመሆኑ ትክክለኛ ማስረጃ መሆናቸውን ማረጋገጥና መረጃውን ለኦዲት ስራው በግብዓትነት መጠቀም አለመቻሉን፣

193. **በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚደረግ የክትትልና ድጋፍ ስራን በተመለከተ፤**

ባለስልጣን መ/ቤቱ በጥበቃ ቦታዎች ለሚሰራው ስራ አጋዥ እንዲሆን የዘረጋው የክትትል የድጋፍና ግብረ መልስ ስርዓት በእቅዱ መሰረት አለመከናወኑና የተሰራውም ቢሆን ያመጣው ውጤት ተገምግሞ በመረጃነት አለመቀመጡን፣

194. **የባለስልጣን መ/ቤቱንና በጥበቃ ቦታዎች ያለውን የሰው ኃይል በተመለከተ፣**

ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ ያሉትን የጥበቃ ቦታዎች ጨምሮ 2,029 በመዋቅር የተፈቀደ የስራ መደብ ያለው ሲሆን አሁን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ግን 971 ብቻ መሆኑና ይህም በመቶኛ ሲሰላ 46.5 መሆኑ፣ በተጨማሪም ረዳት የእንስሳት ሀኪም የሚለው የስራ መደብ በሁሉም ጥበቃ ቦታዎች ላይ መደቡ ክፍት መሆኑ እንዲሁም የታክሲ ደርሚ ባለሙያ በሰው ኃይል መዋቅሩ ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፣

195. **ለሚመለከታቸው የጥበቃ ቦታዎች የተዘጋጀና ወቅታዊ ክለሳ የሚደረግለት የማኔጅመንት እቅድ መኖሩን በተመለከተ፣**

- አዋሽ ፣ አልጣሽ እና ቃፍታ ሽራሮ ብሄራዊ ፓርኮች ፣ ሲንቅሌ ቆርኪዎች መጠለያ እና ባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ የስርዓተ አያያዝ እቅድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣
- ባሌ እና ሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ የስርዓተ አያያዝ እቅዱ ወቅታዊ ክለሳ ያልተደረገበት መሆኑ፣

196. **የጥናትና ምርምር ስራዎች በተመለከተ፤**

ባለስልጣን መ/ቤቱ ከ2010 እስከ 2015እ.ኤ.አ. በዱር እንስሳትና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የጥናትና ምርምር ስራ ለሚሰሩ ለ210 የአገር ውስጥና የውጪ ሀገር ተመራማሪዎች ፍቃድ የሰጠ ቢሆንም በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የሰሩትን ጥናት ሶስት ቅጂ ለባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያስረክቡ ለማድረግ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

197. **በዱር እንስሳቱ መኖሪያ አካባቢ የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶች ከመዘርጋታቸው በፊት የተጽእኖ ግምገማ ስለመሰራቱ እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

በአንዳንድ የጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶች በጥበቃ ቦታው ላይ ለሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽእኖ የተቀመጡ አማራጮች ተግባራዊ አለመደረጋቸው፣

198. **ዳግም ካለሳ ለሚያስፈልጋቸው የጥበቃ ቦታዎች የዳግም ክለሳ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤**

ነጭ ሳር ፣ አሞ ፣ ያንጉዲ ራሳ ብሄራዊ ፓርኮች እና ባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ የዳግም ክለላ ስራ ያልተሰራላቸው በመሆኑ የጥበቃ ቦታውን ዳር ድንበር ከህገ-ወጦች ለማስጠበቅ አዳጋች መሆኑን፣

## 199. በጥበቃ ቦታዎች ሊደረግ የሚገባ የመሰረተ ልማት ዝርጋታን በተመለከተ፤

በአብዛኛዎቹ የጥበቃ ቦታዎች ሊኖር የሚገባ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ የሌላቸው መሆኑና ያሉትም መሰረተ ልማቶች እድሳት ያልተደረገላቸው መሆኑ፣

## 200. የባስልጣን መ/ቤቱን የመረጃ መረብ በተመለከተ፤

የባለስልጣን መ/ቤቱ የመረጃ መረብ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚጎበኝ ቢሆንም ከተግባርና ኃላፊነቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተገቢ መረጃዎች ወቅታዊ እየተደረጉ አለመሆናቸው፣

የሚሉት የተገኙ ሲሆን በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ክፍተቶች ሊያርሙና በአጠቃላይ በዱር እንስሳቱና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የሚሰራውን የልማትና የጥበቃ ስራ ለማጠናከር ያግዛሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

## ክፍል አራት

### የማሻሻያ ሀሳቦች

201. **በጥበቃ ቦታዎች ህገወጥ ተግባራት እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው፤**

ባለስልጣን መ/ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ውስጥ የባለቤትነትን ስሜት ለመፍጠር የሚያስችል ግንዛቤ በመስጠት እና አማራጭ የኑሮ ዘይቤን በመቀየስ በጥበቃ ቦታዎችና በአካባቢው የሚፈጸሙ ህገ-ወጥ ተግባራትን በመከላከል የተጣለበትን ሀገራዊ ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡

202. **የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት ያስቀመጠውን መስፈርት ያሟሉ ስለመሆናቸው፤**

ባለስልጣን መ/ቤቱ ዓለምአቀፋዊ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት ያስቀመጠውን መስፈርት አሟልተው የተቋቋሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች መስፈርቱ እንደተጠበቀ መቆየቱን ሊያረጋግጥ እና የተፋለሱትን ደግሞ እንደገና ወደቀድሞ ይዞታቸው ለመመለስ የተፋለሰውን መስፈርት በመለየት የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

203. **የዱር እንስሳት ሀብትን በተመለከተ፤**

ባለስልጣን መ/ቤቱ በሀገሪቱ በተለይም በጥበቃ ቦታዎች ያሉትን የዱር እንስሳት ቁጥር ትክክለኛ መረጃ እንዲኖረው የተዘረጋውን የቆጠራ ስርዓት ተግባራዊ ሊያደርግና የተደረጉ ቆጠራዎችን ሪፖርት ከየጥበቃ ቦታዎች በወቅቱ በማሰባሰብ አጠቃሎ በመረጃነት ሊጠብቀው ይገባል፡፡

204. **ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ አጥቢ የዱር እንስሳትን በተመለከተ፣**

ባለስልጣን መ/ቤቱ በስጋት ደረጃ (Critically endangered, Endangered, Vulnearable, Conservation, Near threatened and list concern) የለያቸውን አጥቢ የዱር እንስሳት ካሉበት የስጋት ደረጃ ለማውጣት እቅድ ነድፎ በእቅዱ መሰረት የጥበቃና የልማት ስራ ሊሰራባቸው ይገባል፡፡

205. **በበሽታ የተጠቁ አጥቢ የዱር እንስሳት መኖራቸውን በተመለከተ፤**

ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ እየደረሱ ያሉ በሽታዎች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለውን ጥናትና ምርምር በማካሄድ በጥናቶቹ ውጤት መሰረት በሽታ ከመከሰቱ በፊት ሊከላከል እና ሲከሰትም የመቆጣጠር ስራ ሊሰራ ለዚሁም አጋዥ እንዲሆነው በየጥበቃ ቦታው የዱር እንስሳት ሀኪም እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

206. **የባለስልጣን መ/ቤቱን የስራ አመራር አባላት ቃለ-ጉባዔ በተመለከተ፤**

ባለስልጣን መ/ቤቱ መደበኛ እና ተከታታይ የስራ አመራር የውይይት መድረክ ሊኖረው ፣ በውይይቱ ላይ የሚነሱና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት የመፍትሄ እርምጃዎችን ሊወስድ እና ቃለ ጉባኤውን በመረጃነት ሊይዘው ይገባል፡፡

207. **በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚደረግ የክትትልና ድጋፍ ስራን በተመለከተ፤**

ባለስልጣን መ/ቤቱ ለጥበቃ ቦታዎች አጋዥ እንዲሆኑ የዘረጋውን የክትትል ፣ የድጋፍና ግብረ-መልስ ስርዓት በእቅዱ መሰረት በማከናወን ስርዓቱ ያመጣውን ውጤት ሊገመግምና በአካሄድ ያጋጠሙ ክፍተቶችን እየለየ ማስተካከያ ሊሰራ ይገባል፡፡

208. **የባለስልጣን መ/ቤቱንና በጥበቃ ቦታዎች ያለውን የሰው ኃይል በተመለከተ፣**

ባለስልጣን መ/ቤቱ በዋናው መ/ቤትና በስሩ በሚተዳደሩ የጥበቃ ቦታዎች የሰው ኃይል ባለመሟላቱ በአተገባበር ላይ ያመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ ያለመታከት ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ የደሞዝና የጥቅማጥቅሞችን ክፍያ እንዲሻሻል ሊያደርግና በተሟላ የሰው ኃይል ሊሰራ ይገባል፡፡

209. **ለሚመለከታቸው የጥበቃ ቦታዎች የተዘጋጀና ወቅታዊ ክለሳ የሚደረግለት የማኔጅመንት እቅድ መኖሩን በተመለከተ፣**

በጥበቃ ቦታዎች ለሚገኙ የስራ አመራሮች ፤ ለአጥኚዎች ፣ ለለጋሽ ድርጅቶች ለአገር ውስጥና የውጪ ኢንቨስተሮች የተቋቋመበትን አላማ እንዲሁም የአጭርና የረጅም ጊዜ የስራ አካሄድ ምን እንደሚመስል የሚያሳይና የጥበቃ ቦታውን ግብ ለማሳካት የሚያስችል በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ የማኔጅመንት እቅድ ለሌላቸው የጥበቃ ቦታዎች እንዲኖራቸው ያላቸውንም በስራ አካሄድ ላይ ለተፈጠሩ ክፍተቶች ወቅታዊ ክለሳ ሊያደርግ ይገባል፡፡

## 210. የጥናትና ምርምር ስራዎች በተመለከተ፤

ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳትና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ የተሰሩ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በግብዓትነት ለመጠቀም እንዲችል የተቀመጠው መስፈርት ተግባራዊ የሚሆንበትን የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ቀርጾ ሊዘረጋና እንዲተገበር ሊያደርግ ይገባል፡፡

## 211. በዱር እንስሳቱ መኖሪያ አካባቢ የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶች ከመዘርጋታቸው በፊት የተጽእኖ ግምገማ ስለመሰራቱ እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶች ሲኖሩ ከመሰራታቸው በፊት የተጽእኖ ግምገማ ሊደረግና ሲደረግም በሚደረገው ግምገማ ላይ ባለስልጣን መ/ቤቱ እንደባለድርሻ አካል ተሳታፊ በመሆን ለተግባራዊነቱ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

## 212. ዳግም ካለላ ለሚያስፈልጋቸው የጥበቃ ቦታዎች የዳግም ክለላ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፣

ባለስልጣን መ/ቤቱ የድንበር ማካለል ስራ ያልተሰራላቸውን የጥበቃ ቦታዎች በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ድንበሩ ከህገ-ወጦች እንዲጠበቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡

## 213. በጥበቃ ቦታዎች ሊደረግ የሚገባ የመሰረተ ልማት ዝርጋታን በተመለከተ፤

በጥበቃ ቦታዎቹ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የመሰረተ ልማት ዝርጋት ቢኖር የጥበቃ ቦታው ለአገር ውስጥና ለውጪ ሀገር ቱሪስቶች የሚሰጠውን አገልግሎት የተሟላና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ የአገሪቱን ጠቅላላ ኢኮኖሚ ከማሳደግ አንጻር ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በዘርፉ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራበት ይገባል፡፡

## 214. የባስልጣን መ/ቤቱን የመረጃ መረብ በተመለከተ፤

ባለስልጣን መ/ቤቱ ከተቋቋመበት አላማ አንጻር በዘርፉ የተሰሩ እና ሊሰሩ ያሉ ስራዎችን የዱር እንስሳቱን እና የመኖሪያ አካባቢያቸውን ገላጭ በሆነ መልኩ በምስልና በጽሁፍ በማስቀመጥ ለአገር ውስጥና ለውጪ ሀገር ተጠቃሚዎች ሀገር የማስተዋወቅ ስራ

ሊሰራበት እንዲሁም በመስኩ ሊሰማሩ የሚችሉ አጋሮችና ባለሀብቶች ሊጋበዙበት ይገባል፡፡

ለማጠቃለልም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የጥበቃ ቦታዎች በተለያየ መልኩ ለሰው ልጅ በህይወት መኖር አንድ ምክንያት በመሆናቸውና የአገሪቱን ገጽታ ለአለም ከማስተዋወቅና የአገሪቱን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ ከማሳደግ አንጻር ያላቸው ሚና የጎላ በመሆኑ ለዚሁ ተግባር ኃላፊነት የተጣለበት የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመስራት፡-

- የአገር ውስጥና የውጪ ሀገር ባለሀብቶች በዘርፉ መዋእለ-ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር፣
- ባለሀብቶቹም ሲመጡ መስፈርት አዘጋጅቶ በጥበቃ ቦታዎቹ የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ አስገዳጅ ሁኔታን ሊፈጥር፣
- በጥበቃ ቦታዎች ሊሟሉ የሚገባቸውን መሰረተ ልማቶች በማሟላት የአገልግሎት ክፍያዎችን ሊያሳድግ፣
- በጥበቃ ቦታዎች የሚገኘውን ማህበረሰብ የጥበቃ ቦታው ተጠቃሚ በማድረግ የባለቤትነት ስሜት ሊፈጥር፣
- በጥበቃ ቦታዎች የሚደረግ የጥበቃ ሥራ ዳግም ለሰው ልጅ ሕይወት ህልፈት ምክንያት እንዳይሆን ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት ሊሰራ፣
- ከባለስልጣን መ/ቤቱ አቅም በላይ የሆኑና የአሰራር ክፍተት የፈጠሩበትን ጉዳዮች በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ አፈጻጸም እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣንና መረጃ የተሰበሰበባቸው በናሙና የተመረጡ የጥበቃ ቦታ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

**አባሪ 1**

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

## Audit Issues and Evaluative Criterias

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/ | የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. ባለስልጣን መ/ቤቱ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ልማትና ጥበቃ በወጡ ህጎች ፣ መመሪያዎች ፣ አለም አቀፍ እና አገር አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ቀልጣፋ እና ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤ | 1.1. ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ሊያለማ፣ ሊያስተዳድር፣ እና ህገ-ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙባቸው ሊከላከል ይገባል፡፡ |
| | 1.2. ባለስልጣን መ/ቤቱ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በዓለም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት እንዲመዘገቡ ለማስቻል ዓለማቀፋዊ መስፈርት ማሟላታቸውን ሊያረጋግጥ እና እነዚህኑ መስፈርቶች ተጠብቀው መተዳደራቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 1.3. ባለስልጣን መ/ቤቱ የዱር እንስሳት ሀብትን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት ወቅታዊ ሪፖርት እያዘጋጀ ሊልክ ይገባል፡፡ |
| | 1.4. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎች ላይ ጥናትና ምርምር በማካሄድ በጥናቶቹ ውጤት መሰረት ሊከላከል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | 1.5. ባለስልጣን መ/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድ ሊያቅድ እንዲሁም በየበጀት አመቱ ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ሊያቅድ ይገባል፡፡ |
| | 1.6. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየበጀት አመቱ አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያዘጋጅና በእቅድ ተይዘው ተግባራዊ |

| | |
|---|---|
| | ያልተደረጉ ስራዎችን መንስኤያቸውን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 1.7. ባለስልጣን መ/ቤቱ መደበኛ እና ተከታታይ የስራ አመራር የውይይት መድረክ ሊኖረው እና በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ በመያዝ ተከታታይ ቁጥር ሰጥቶ በአግባቡ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 1.8. በባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል በሚገኙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ የሚሰራው የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ስራ በተያዘለት ጊዜ መሰረት ሊከናወንና አፈጻጸሙ በሪፖርት የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 1.9. ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል የሚገኙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ የተሰማሩ አስፈጻሚዎች ጊዜውን የጠበቀ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከታቸው የባለስልጣኑ ኃላፊዎች ማቅረባቸውን ሊያረጋግጥና አፈጻጸማቸውን ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | 1.10. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሀገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብት በአይነት ፣ በቁጥርና በመኖሪያ አካባቢ ለማወቅ የሚያስችለው አገራዊ የዱር እንስሳት ቆጠራ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.11. ህልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡ የዱር እንስሳት ንግድ የህግ ማዕቀፍን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 1.12. ባለስልጣን መ/ቤቱ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ስራውን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችለውን የተሟላና ቦታውን የሚመጥን ባለሙያ (የሰው ኃይል) በመዋቅሩ መሰረት ሊያሟላ ይገባል፡፡ |
| | 1.13. ባለስልጣኑ በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚኖረውን ህብረተሰብ ወቅታዊ ፍላጎት በማጥናት አመታዊ እቅድ |

| | |
|---|---|
| | ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ |
| | 1.14. ባለስልጣኑ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና ተጨማሪ የሀብት ምንጮችን በማፈላለግ በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ለሚኖሩ ህብረተሰብ ክፍሎች አማራጭ የአኗኗር ስልቶችን መቀየስ ይኖርበታል፡፡ |
| | 1.15. ባለስልጣኑ በነባርና በአዲስ መልክ የሚቋቋሙትን የጥበቃ ቦታዎች በአለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት (IUCN) መስፈርት በሚያዘጋጀው ብሄራዊ ቴክኒካል ማኑዋል መሰረት በመገምገም የጥበቃ ቦታውን አይነት መወሰን ይኖርበታል፡፡ |
| | 1.16. ባለስልጣኑ ሁሉንም ባለድርሻዎች ባሳተፈ መልኩ አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ መርሆዎችን የተከተለ የመሰረተ ልማት የማኔጅመንት ፕላን እንዲዘጋጅ በማስተባበር በየጊዜው ማሻሻል እና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ |
| | 1.17. ባለስልጣኑ የዱር እንስሳቱን መኖሪያ ቦታ ሊቀንሱ የሚችሉ መጤ እና ወራሪ ዝርያዎችን ፤ የቁጥቋጦ መስፋፋትንና የሰደድ እሳትን መከላከል ፤ በቀላሉ ሊጎዱ የሚችሉ ስርዓተ-ምህዳሮች(Fragile ecosystem) ክትትል በማድረግ ተገቢውን የአያያዝ ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ |
| **2. ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች አይነት ፣ ብዛት እና የመኖሪያ አካባቢ /ሥርዓተ-ምህዳርን/** | 2.1. ለጥናትና ምርምር ፍቃድ ያገኙ አጥኚዎች ጥናታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱን መመሪያ የተከተለ ስለመሆኑ በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 2.2. ባለስልጣን መ/ቤቱ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ አጥቢ የዱር እንስሳትን ለመለየት ጥናት ሊያካሂድና በውጤቱ መሰረት የማልማትና የጥበቃ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችል የጥናትና ምርምር ስራ መሰራቱንና ጥናቱ ያመጣው ውጤት የሚመዘንበት ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን መገምገም፤ | 2.3. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ችግሮች ያሉባቸውን የጥበቃ ቦታዎች በመለየት እንደችግሩ ክብደት በቅደም ተከተል አስቀምጦ ችግሮችን በወቅቱ ሊፈታ ይገባል። |
| | 2.4. ባለስልጣን መ/ቤቱ ያሉትን የጥበቃ ቦታዎች መልሶ ለማልማት ፣ አዳዲስ የጥበቃ ቦታዎችን ለማቋቋምና ዳግም ክለላ ለሚያስፈልጋቸው የጥበቃ ቦታዎች እንደገና ለማካለል እቅድ ሊይዝና በእቅዱ መሰረት ሊሰራ ይገባል። |
| | 2.5. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ አጥቢ የዱር እንስሳት አይነት፣ ብዛትና ስርጭት ለማወቅ የሚያስችለውን ጥናት ሊያደርግ ይገባል። |
| | 2.6. ባለስልጣን መ/ቤቱ የዱር እንስሳት አደን ኮታ ለማውጣት እንዲያስችለው በየሶስት አመቱ የታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራ በህጋዊ ቁጥጥር አደን ቀበሌ ሊያደርግ ይገባል። |
| | 2.7. በየጊዜው ለሚካለሉ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች መስፈርት ሊቀመጥለትና ክለላው መስፈርቱን ያሟላ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል። |
| | 2.8. የክለላ መስፈርት አሟልተው የሚካለሉ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ከተካለሉበት አላማ ጋር የሚቃረን ስራ የማይሰራበት ሊሆን ይገባል። |
| | 2.9. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የማያሳድር በእቅድ ላይ የተመሰረተ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ሊደረግ ይገባል። |
| 3. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘና ወቅታዊ የሆነ የመረጃ | 3.1. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ላይ የሚሰራውን የልማትና ጥበቃ ስራ በመረጃ መረቡ ላይ ሊያስቀምጥና ወቅታዊ ሊያደርገው ይገባል። |
| | 3.2. ባለስልጣን መ/ቤቱ ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ |

| | | |
|---|---|---|
| | **አሰባሰብ ፣ አስተዳደርና ስርጭት ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤** | የዱር እንስሳትን የሚመለከቱ ሰነዶች ሊኖሩት ይገባል፡፡ |
| | | 3.3. ቁጥራቸው በመመናመን ላይ ያሉ አጥቢ የዱር እንስሳትን ለማልማት የተሰሩና እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን የሚያሳዩ መረጃዎች በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊኖሩ ይገባል፡፡ |
| | | 3.4. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየጥበቃ ቦታዎች የሚደረጉ የዱር እንስሳት ቆጠራ ሪፖርቶችን በወቅቱ አጠናቅሮ በመረጃነት ሊይዛቸው ይገባል፡፡ |
| | | 3.5. በጥበቃ ቦታዎች የሚደረጉ የመስክ ጉብኝት ሪፖርቶች ተጠናቅረው በባለስልጣን መ/ቤቱ በመረጃነት ሊቀመጡ ይገባል፡፡ |
| | | 3.6. ባለስልጣኑ እንደ የስጋት ደረጃቸው ትኩረት የሚሹ አጥቢ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ላይ ለመስራት እንዲያስችለው Critically endangered, Endangered, Vulnearable, Conservation, Near threatened and list concern ውስጥ ያሉት አጥቢ የዱር እንስሳት እነማን እንደሆኑ ወቅታዊ የሆነ ዝርዝር መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | | 3.7. ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፍቃድ አግኝተው የጥናትና ምርምር ስራ የሰሩ የአገር ውስጥና የውጪ አገር ተመራማሪዎች ዝርዝርና የሰሩት የጥናትና ምርምር ስራ በባለስልጣን መ/ቤቱ በመረጃነት ሊጠበቅ ይገባል፡፡ |
| 4. | **ባለስልጣኑ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥና በአካባቢው ለሚገኘው ህብረተሰብ እና በየደረጃው ላሉ** | 4.1. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ለሚኖሩ ህብረተሰቦች የዱር እንስሳቱን በመጠበቅ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የግንዛቤ መስጫና አሳታፊ የውይይት መድረኮችን ሊያዘጋጅ እና መድረኩ ያመጣውን ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | | 4.2. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጥበቃ ቦታዎች ላይ በተለያየ መንገድ ጉዳት የሚያደርሱ ህገ-ወጦችን ለመከላከልና |

| | |
|---|---|
| **ባለድርሻ አካላት የስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ *ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ በማድረግ ያመጣውን ውጤት የሚገመግም መሆኑን ማረጋገጥ፤*** | የዱር እንስሳቱን ከአደጋ ለመከላከል እንዲያስችለው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ የቅንጅት ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 4.3. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላትና ከማህበረሰቡ ጋር የሰራውን ስራና ያመጣውን ውጤት የገመገመበት መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 4.4. ባለስልጣኑ ወቅታዊ የትምህርት ማኑዋሎች እንደ አስፈላጊነቱ ፊልሞች ፣ ፖስተሮች በመሳሰሉት የትምህርት መስጫ ዘዴዎች በመታገዝ እንደየደረጃው ለአስጎብኚዎች ፣ ለባለሙያ አሳዳኞች ፣ ለህግ አስፈፃሚ አካላት ለስራ ሃላፊዎች ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችና በማስልጠኛ ማዕከላት ለሚገኙ የመከላከያ ሀይል አባላት ፣ ለት/ቤቶች ፣ ሕዝባዊ ማህበራትና በአገሪቱ የመግቢያና የመውጫ በሮች ኬላ ላይ ቁጥጥር ለሚያደርጉ ሰራተኞች የዱር እንስሳት ጥበቃ ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ትምህርቱን መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ |
| | 4.5. ባለስልጣኑ ለቅድመ መከላከያ እርምጃ ያመች ዘንድ የግጭት መከላከያ ዘዴዎችን የያዙ ማኑዋሎችን መፅሄቶችን በራሪ ፅሁፎችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ማሰራጨት ይጠበቅበታል፡፡ |
| | 4.6. ባለስልጣኑ በዱር እንስሳት ስነ-ህይወት ፣ ስነ-ምህዳርና ጤና ዙሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት እና ጥቅም ላይ ማዋል ይኖርበታል፡፡. |